# አባባይ መናፍስቶች

እንዴት አደራችሁ፡ ወዳጆቼ። ዛሬ ጠዋት እዚህ በመገኘቴ፡ ሁላችሁንም እዚህ በማየቴ ደስ ብሎኛል፡ ጌታ ዛሬ ከእኛ ጋር መሆኑን በማመን፡ እዚህ ተብርናክል ውስጥ ለጠዋት አገልግሎት በጣም ሞቃት እንዳይሆን፡ ትንሽ ጥላ በመስጠቱ በጣም ደስ ብሎኛል። አሁንም እኛ...

2 ልጆች፡ ያሉ ይመስለኛል... ወንድም ኔቪል፡ ልጆቹ ወደ ክፍሎቻቸው ሄደዋል´ዴ? አንዳንድ ህጻናት አይቻለሁ፡ ወደ ሌላ ክፍላቸው፡ ወደ ሰንበት ትምህርት ክ—ክፍላቸው ተመልሰው ገብተው ይሆንን ብዬ ነው።

3 አሁን፡ ጸልዩልኝ። ትናንት ማታ ማድረግ የነበረብኝ ትልቅ ውሳኔ አለ፡ እና ዛሬ መወሰን አለብኝ። ቤተ ክርስቲያንም ትጸልይ። ቀጣይ አ—አንድ ሰብሰባ አለኝ፡ ሰብሰባው የሚካሄደው በጀርመን አገር አይረን ከርተይን በተባለው መስመር ስለሆነ፡ ትንሽ ጥንቃቄ ይጠይቃል። እና ጸልዩልኝ። ስለዚህም፡ በጀርመን ውስጥ ሂትለር ከጦርነቱ በፊት በሠራው፡ በዚያ ትልቅ የክሪኬት ስታዲየም፡ ወዲያውኑ መጀመር እንችላለን፡ ጥሩ ትልቅ ቦታ ነው፡ ሰማንያ ሺህ የሚያስተናግድ መቀመጫ አለው። ለአስር ተከታታይ ምሽቶች፡ ልንይዘው እንችላለን። በዚያም ወዲያውኑ ለመጀመር ተስፋ እናደርጋለን፡ ከዚያም ወደ ላ ሳሌ ሎሬይን፡ ፈረንሳይ፡ ቀጥሎም፡ ወደ በርሊን፡ ማ... ማለቴ፡ በርሊን በ—በዚያና በፈረንሳይ መካከል ያለችው።

4 ከዚያም ጌታ ቢፈቅድ፡ ወደ ቺካጐ ኮንቬንሽን፡ እንመለሳለን። የእኔ ተራ በአምስት፡ በስድስት፡ በሰባት፡ በስምንተኛውና፡ በዘጠነኛው ቀን፡ የሚጀምር፡ ይመስለኛል፡ በቺካጐ በሚገኘው፡ በ—በስዊድን ቤተክርስቲያን ሰብሰባ ላይ በእነዚህ ቀናት እሳተፋለው። ከዚያም እነ፡ አቶ ቦዜ፡ ከቺካጎ አከባቢ የሆናችሁ አንዳንዶቻችሁ፡ ከነሐሴ ወር መጀመሪያ፡ ወ... ወይም ከመስከረም ወር መጀመሪያ ጀምሮ፡ በስዊድን ውስጥ፡ ሰብሰባ አላቸው። ወደዛ እንድመጣ፡ መቶ በመቶ፡ ሁሉም ሰው እኔን ስለመረጠኝ ዓለም አቀፋዊ ስለሆነም በጣም ደስ ብሎኛል። በዛ በጣም ደስተኛ ነኝ፡ ነገር ግን ወደዚያ ወይም ወደዚህ መሄድ አለብኝ። ጌታ ብዙ ነፍሳት ወደሚድኑበት ቦታ እና ለእግዚአብሔር መንግሥት፡ የተሻለ ነገር ወደምሆንበት ቦታ በትክክል እንዲመራኝ ጸልዩልኝ። አሁን፡ እነሱ እዚያ፡ በ—በስዊድን ውስጥ ኮንቬንሽን አላቸው፡ በሰብሰባው መጀመሪያ ሀያ-አምስት፡ ሠላሳ-አምስት ሺህ ያህል ሰው ተገኝቶልናል፡ ብዙዎቹም ያልዳኑ ናቸው ብሏል።

5 ከዚያም በጀርመን ውስጥ ደግሞ፡ እንግዲህ፡ ሰማንያ ሺህ መቀመጫዎች ያሉት ስታዲየም አዘጋጅተዋል። እርግጥ ነው፡ እኛ፡ አሁን ሰዊዘርላንድ በሄድንበት፡ ድንቅ ሰብሰባ አድርገናል፡ ምናልባትም ብዙዎቻችሁ እስካሁን አልሰማችሁትም። በ—በ—በዙሪክ፡ ሰዊዘርላንድ፡ ጌታ እጅግ ባርኮናል፡ በአምስት ምሽቶች ውስጥ ሐምሳ ሺ ሰዎች ጌታን ተቀብለዋል።

6 ከዚያም፡ ወንድም ጃክ ሹለር፡ ብዙዎቻችሁ ታውቁታላችሁ፡ ሜቶዲስት ነው፡ የሽማግሌው የቦብ ሹለር ልጅ ነው። እነሱ አሁን ቤልፋስት ውስጥ

ናቸው፡ እ—እነርሱም ያን ቦታ፡ ቢሊ ግራሃም፡ በሰብሰባው ካደረገው፡ የበለጠ ለወንጌል እየነቀነቁ እንደሆነ ተናግረዋል። ጃክ በቅናት በፍቅር የተሞላ፡ በጣም ጥሩ ወጣት ነው። እ—እርሱም በጣም ቅን የሆነ ሰው ታላቅ የጌታ ባሪያ መሆኑን አምኜበታለሁ። ለወንድም ሹለር ጸልዩ። ጃክ ሹለር፡ ጃክ ማካርተር—ደግሞ ከእርሱ ጋር ነው። ወንድም ጃክ ማካርተርም፡ ታላቅ ሰባኪ ነው። የሃይማኖት አባቶችም አይርላንድን ያጋጠማት ታላቅ መነቃቃት ዋናው እንደሆነ ይናገራሉ። ስለዚህ እኛ… ለ—ለእነዚያ ሰዎች በየቀኑ ጸሎት እናደርጋለን። ሁለቱም ወጣቶች ናቸው፡ ዕድሜአቸው፡ አርባ አከባቢ ነው፡ ብዬ እገምታለው፡ ወይም ከዛም በታች፡ ቤተሰቦች እና የመሳሰሉትም፡ ጥሩ ጠንካራ የወንጌል አስተማሪዎች ናቸው፡ እነወዳቸዋለን።

7 አሁንም፡ እንዳትረሱኝ እ—ጸልያለሁ፡ እግዚአብሔር አሁን ትክክለኛውን ውሳኔ እንዳደረግ ይ—ይርዳኝ። የትኛውን አቅጣጫ መሄድ እንዳለብህ የማታውቅበት ጊዜ አለ። በእንደዚህ አይነት ሁነታ ገብታችሁ ታውቃላችሁ? ጳውሎስም በእንደዚህ ዓይነት አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ የሚያውቅ ይመስለኛል፡ አይደል? በሁለት ጠባባብ መካከል ነው። በጉዞ ሳለ፡ እነሆ፡ “ወደ መቄዶንያ ተሻገር፡” የሚል መልዕክት የሰጠውን መልአክ በራእይ ተመልክቷል። ስለዚህ ልክ እንደ ጳውሎስ በልቤ ሰለ እሱ ትሁት መሆን ከቻልኩኝ፡ ጌታ አሁንም መልአክ አለው። አይደል?

8 አሁንም፡ ዛሬ ምሽት፡ የመጣችሁ ሁላችሁ፡ በተብርናክሉ ውስጥ ያለውን የወንጌል አገልግሎት አትርሱ። በሉዊሰቪል ዙሪያ ያላችሁ፡ ዛሬ ማታ፡ ከሰባት ተኩል እስከ ዘጠኝ ተኩል፡ ለጥቂት ሰዓታት በወንድም ካውብል ቤተክርስቲያን፡ መገኘት-ለሚፈልግ ሁሉ፡ በሩን-ክፍት አድርጌ ነው የምሰብከው። እዚህ ለሁለተኛ ጊዜ እመጣለሁ ብዬ ነበር። በጣም ጥሩ ሰው ነው፡ እርሱም ጠራኝ። ወንድም ካውብል፡ በጣም ጥሩ፡ ወንድም ነው። እንደምትተዋወቁ፡ እርግጠኛ ነኝ፡ በጣም መልካም ወንድም፡ ምንም እንዳልሆነ እንዲሁ ትታችሁት መሄድ አያሰችላችሁም። ጸልዩ። ከሁሉም በላይ ጸልዩ፡ ጸልዩ፡ እግዚአብሔርም ትክክለኛውን ውሳኔ እ—እንድናደርግ እንዲሰጠን ጸልዩ።

9 አሁን፡ የወንጌል መልዕክቱን ከመጀመራችን በፊት፡ ዛሬ ትናንሽ ልጆችን ለጌታ አደራ የምንሰጥበት ማለዳ ነው። እዚህ ጋርም፡ ለጌታ አደራ የምሰጠው፡ ብላቴና ይዣለሁ። አሁን፡ ብዙ ጊዜ በብዙ ቸርቾች…

ከኋላ ያላችሁ፡ በደንብ ይሰማችኋል? ይሰማችኋል፡ መልካም ነው? እነዚህ ማቀዝቀዣዎች፡ እንደው፡ ራሳችሁን መሰማት አትችሉም። አይ፡ ይሁን፡ ችግር የለውም። ያለነሱ እጠፋለሁ ብዬ እፈራለሁ።

10 ስለዚህ—ህጻናትን፡ አንዳንድ ጊዜ፡ ገና ሚጢጢ ሆነው፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ይረጩባቸዋል። እርግጥ ነው፡ ይህ የመጣው፡ ከካቶሊክ ነው፡ ገና ህጻናት ሆነው ሳሉ፡ “ጥምቀት” ወይም ክርስትና ማስነሣት ይሉታል። የሜቶዲስት ቤተክርስትያን የሕፃናት ጥምቀት፡ እና ሌላም፡ ብዙ ተጨማሪ ነገሮች፡ ይዛ ወጣች። እንደሚመስለኝም በናዝሪን እና በጥንታዊ-ሜቶዲስት መካከል ያላቸው ልዩነት፡ የሕጻናት ጥምቀት፡ እና የመሳሰሉ ጥቃቅን ነገሮች ይመስለኛል። ነገር ግን፡ ምንም ይሁን ምን፡ ዋናው ይህ አይደለም፡ ብዙም

ለውጥ አያመጣም። ምክንያቱም፡ ምንም ቢሆን፡ ሁሉም ነገር፡ ቀራንዮ ራሱ፡ በትክክል የገለጸው፡ ይመስለኛል፡ ኢየሱስ የሞተውም ህጻናትን ለማዳን እና ዓለምን ለማዳን ነው።

11 እና ህጻን ልጅ፡ ወላጆቹ ምንም ቢሆኑ፡ ኃጢአተኞች ቢሆኑም፡ ምንም ለውጥ አያመጣም፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነጽቷል፡ እያችሁ፡ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግም እርሱ ነው። ይህ ሕፃን ንስሐ መግባት አይችልም። ንስሐ መግባት እንዴት እንደሚቻል አያውቅም። እዚህ ለመገኘቱ፡ የራሱ የሆነ ምክንያት የለውም። ለምን እንደመጣ ሊነግራችሁ አይችልም። ያመጣው እግዚአብሔር ነው፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ደምም ወደ ዓለም በመጣበት ቅጽበት አነጻው። ይህም እስከ ተጠያቂነት ዕድሜ ድረስ ነው፡ ከዚያም ክፉና መልካምን ያውቃል፡ ይህን ባወቀ ጊዜም ክፉ ማድረጉን ላወቀው ነገር ንስሓ ይገባል። ያ ትክክል ነው። ስለዚህ፡ አንዳንዶቹ ይረጩታል፣ እናም ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደማይሄዱ ያስባሉ።

12 እንዲህ የሚል ትምህርት ደግሞ አለ ህጻኑ መንፈስ ቅዱስ ከተሞሉ ወላጆች ከተወለደ፡ እንግዲህ፡ ህጻኑ ወደ ገነት ይሄዳል፥ ካልሆነ፡ ግን፡ አይገኝም፡ ህጻኑ ልጅ ከህልውና ይጠፋል። ይህ ሙሉ በሙሉ ስሕተት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ወላጆች መሆናቸው ምን ለውጥ ያመጣል? ሁሉ ከጾታዊ ምኞት ነው፡ ሕፃኑም በተመሳሳይ መንገድ ተወለደ። ስለዚህ፡ ሁሉም "በኃጢአት የተወለዱ፡ በዓመጽ የተረገዙ፡ ውሸት እየተናገሩ ወደ ዓለም የመጡ ናቸው።" ይህም፡ መጽሓፍ ቅዱሳዊ ቃል ነው።

13 ስለዚህ፡ ከዚያ በኋላ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ያንን ልጅ ያነጻዋል እንዲሁም ያስተስርይለታል። በዓለም በጣም ኃጢአተኛ በተባሉ ወላጆች፡ ቢወለድ እንኳ፡ ክፉን እና መልካምን መለየት እስኪችል ድረስ፡ ቢሞትም እንኳ ወደ እግዚአብሄር ህልውና ይገባል። ከዚያ በኋላ ለሚሰራው ሁሉ፡ ምን ያደርጋል፡ ስለ ሰራው ምሕረት ይለምናል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የግሉን ንስሐ ይገባል። ህፃን ሳለ ግን...

14 አሁን፡ በዚህ ተበርናክል፡ ለመከተል የምንሞክረው መንገድ ይህ ነው። በዓለም ላይ እኔ ሄጄ ዶክትሪን የምሰብክበት፡ ብቸኛው ቦታ፡ እዚህ ተብርናክል ውስጥ ነው፡ ምክንያቱም ይህ ቤተክርስቲያናችን ነው። ሕዝቡንም በትክክለኛው መንገድ ለመጠበቅ እዚህ ዶክትሪን እንሰብካለን። ሌሎች ሰዎችም፡ በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ፡ የሚያምኑትን ሁሉ ይሰብካሉ። እነርሱም ወንድሞቼ ናቸው፡ ትንሽ ልንለያይ እንችላለን፡ ግን አሁንም ያው ነው ወንድማማቾች ነን። ይሁን እንጂ፡ እዚህ ተበርናክል ውስጥ፡ የምንሰብከው መጽሓፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንደሆነ እናስባለን። በዚያም፡ አደራ መስጠት ብለን የምንጠራው፡ የልጆችን አደራ መስጠት፡ የምናየው፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ብቸኛው ጊዜ፡ ወይም በአዲስ ኪዳን ውስጥ በሕጻናት ላይ ሲደረግ ያየነው ነገር፡ ወይም ክርስቶስ በሥነ ሥርዓቱ ውስጥ ያደረገው ነገር፡ ቢኖር፡ ኢየሱስም ሕፃናቱን አንሥቶ እጁን ሲጭንባቸው እና ሲባርካቸው፡ "ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ። አትከልክሏቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና፡" ሲላቸው ነው።

15 አሁን፡ እንደምንረዳው፡ እርሱ ሊ—ሊፈፅመው የመጣውን ሥራ፡

ለመቀጠል የቀረነው እኛ ነን። በቀራንዮ ላይ የሞተው፡ ከእግዚአብሔር ወጥቶ… ወደ ዓለም መጣ፡ ከእኛ ጋር ነበር፡ ከእኛም ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ ሄደ፡ ወይም ከዓለም ወደ እግዚአብሔር ተመለሰ፡ እንደገናም በመንፈስ ቅዱስ አምሣል መጣ፡ አሁንም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ከእኛ ጋር፡ በእኛ ውስጣችንም አለ፡ ያኔ በምድር በነበረ ጊዜ ያደረገውን ተመሳሳይ ሥራ እየሰራ በገዛ ቤተ ክርስቲያኑ ይገኛል። በዚህም መንገድ፡ ልጆቻችንን፡ ከአንዱ ሌላው በማከታተል፡ ለአገልጋዮቹ እናቀርባለን፡ እነሱም ይጸልዩላቸዋል፡ በላያቸው ላይ እጃቸውን ይጭናሉ ለእግዚአብሔርም አሳልፈው ይሰጣሉ። ጌታ ለእኛና ለህጻናት ላደረገው ነገር አድናቆታችንን ለመግለጽ ትንሽ ሥነ ሥርዓት እናደርጋለን።

16 አሁን፡ ህጻን ልጃችሁ በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ቢረጩት፡ ወይም ሌላ ነገር፡ እሰቲ እሰቡት። በዚህ ላይ ምንም ነገር አንቃወምም። ምንም ችግር የለውም። ነገር ግን፡ በቅዱሳት መጻሕፍት መሠረት፡ ኢየሱስ ራሱ፡ የባረካቸው ቦታ፡ አንድ ቦታ ብቻ እናገኛለን። እዚህ ቃሉ ው—ውስጥ፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ እነበዋለው። በቅዱስ ሉቃስ፡ እናገኘዋለን… እ—አሰረኛው ምዕራፍ ይመስለኛል፡ ከ13ኛው ቁጥር ጀምሮ።

> **እንዲዳስሳቸውም ሕፃናትን** ወደ **እርሱ አመጡ፡ ደቀ መዛሙርቱም፡** ያመጡአቸውን **ገሠጹአቸው።**
>
> **ኢየሱስ ግን አይቶ፡ ተቈጣና፡ እንዲህም አላቸው፡ ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ፡ አትከልክሉአቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና።**
>
> **እውነት እላችኋለሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት፡ ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው።**
>
> **አቀፋቸው፡ እጁንም** ጭኖ፡ **ባረካቸው።**

17 እንዴት ያለ ፍቅር ነው? እንዲህ አለ፡ "አሁን፡ ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተውአቸው። አትከልክሉአቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ እንደነዚህ ላሉት፡ ለህጻናት ናትና።" አቀፋቸው እና ባረካቸው።

18 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት፡ እንዲህ ቢሆንልን ምንኛ ደስ ይላል፡ ኢየሱስ በዚህ መድረክ፡ በአካል ብናገኘውና፡ "ጌታ ሆይ፡ እባክህ ልጄን ባርክልኝ፡" ብንለው፡ ምንኛ በወደድን? ኦህ፡ ዓይናችን እና ልባችን ይህን ለማየት… ምንኛ ይናፍቃል። ይሁን እንጂ እንድንሰራለት ተልዕኮውን ለእኛ ሰጥቶናልና፡ አሁንም ቢሆን፡ እዚህ አለ። እንዳደረግነውም፡ እንዲሁ፡ እውቅና ይሰጣል። የላካቸውን እንቀበላቸዋለን፡ እርሱን የላከውን ተቀበሉት፡ አያችሁ። ስለዚህ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ አለ። ከቻለች እኅት ገርቲ መጥታ ከረጅም ጊዜ በፊት እንዘምር የነበረውን የድሮ መዝሙር በፒያኖው ብትጫወት መልካም ነው፡ እንዲህ የሚለውን፡ "አምጧቸው፡ ህጻናትን ወደ ኢየሱስ አምጧቸው።" መጽሐፉ ውስጥ ያለ ይመስለኛል። እርግጠኛ አይደለሁም። "ህጻናትን ወደ ኢየሱስ አምጧቸው።" ሕፃን ልጅ፡ ገና ለጌታ አደራ ያልተሰጠ ሕፃን ካላችሁ፡ ዛሬ ጠዋት አደራ መስጠት ከፈለጋችሁ፡ ታዲያስ፡ እኛ በደስታ እናደርገዋለን።

19 በዚህም ሕንጻ ውስጥ አገልጋዮች ካላችሁ፡ ሰባኪዎች የሆናችሁ እነዚህን ልጆች ለጌታ አደራ አሳልፈን ስንሰጣቸው መጥታችሁ ከእኛ ጋር መቆም

የምትፈልጉ ካላችሁ? መምጣታችሁ፡ ደስ ይለናል። መልካም፡ በዚያ በመጽሓፉ ውስጥ አለ? አገኘኸው፡ ወንድም ነቪለ? በዚያ የለም። መልካም፡ **አምጧቸው** የሚለውን፡ ስንቶቻችሁ ታውቁታላችሁ? መልካም፡ እንዘምረው። እናቶች ልጆቻቸውን እያመጡ፡ በአንድነት እንዘምር። መልካም። መልካም።

… አምጧቸው፡ አምጧቸው፡
ከኃጢአት ሜዳ አምጧቸው፡
አምጧቸው፡ አምጧቸው፡
ተቅበዝባዡ ወደ ኢየሱስ አምጧቸው።

አምጧቸው፡ አምጧቸው፡
ከኃጢአት ሜዳ አምጧቸው፥
አምጧቸው፡ አምጧቸው፡
ህጻናትን ወደ ኢየሱስ አምጧቸው።

ለአፍታ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

20 የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት እናቶችና አባቶች አንተ በቸርነትህ የሰጣሃቸውን ፍሬዎች በእጃቸው ይዘው እና በእቅፋቸው አርገው፡ እነሆ በመሰዊያው ዙርያ ቆመዋልና። ጌታ ሆይ፡ ስለ እነሱ እጅግ ያመሰግኑሃል፡ ዛሬ ጠዋትም በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ፡ ሕይወታቸውን ለአንተ አሳልፈው ለመስጠት፡ ወደዚህ ወደ መሠዊያው፡ አምጥተዋል። አንተው ሰጠሃቸው። እግዚአብሔር ሆይ፡ እያንዳንዳቸውንም እንድትመግባቸውና እንድትባርካቸው፡ እንጸልያለን። ምራቸው፡ የእግዚአብሔርም ጠባቂ መላእክት እያንዳንዳቸውን ይጠብቃቸው። ረጅም እድሜ እና ደስታን ስጣቸው። ነገ ካለ፡ ለነገ የሚያድጉ፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ይሁኑ።

21 ጌታ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት በመሠዊያው ዙሪያ ካሉት ሕፃናት መካከል ሰባኪዎች ነቢያትና አስተማሪዎች እንዲነሱልን እንጸልያለን። አርጅተንም ከዚህ በላይ መሄድ በማንችልበት ጊዜ፡ አንድ ሰው ከቦታ ወደ ቦታ ሊወስደን ይገባል፡ ዛሬ እዚህ ባሉት የሚሰበከውን ወንጌልን ቆመን መሰማት መቻል ይሁንልን። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። በአንድ በክብር ቀንም ሁሉም ነገር ሲያበቃ፡ ሕይወታችን ሲጠናቀቅ፡ እነዚህ ወላጆች በመሠዊያው ዙሪያ ያሉት፡ እንደ ጥንታዊው ያዕቆብ ልጆቹን ሁሉ እንደባረካቸው በዘመን ፍጻሜ መጨረሻቸው ምን እንደሚሆን ነግሯቸው እንደነበረው ልክ እንደዛው ይሁንልን። ከዚያም ቀና ብሎ፡ እንዲህ አለ፡ "እነሆ፡ ከወገኖቼ ጋር እሰበሰባለሁ።" በተወደደች ቀን፡ እሱና ዘሮቹ፡ በተሻለች ምድር ላይ ይሰበሰባሉ። በለዓም፡ "ፍጻሜዬ እንደ እርሱ ይሁን" ማለቱ ምንም አያስደንቅም። እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚህን በረከቶች በወላጆች ላይ ይሁን ብዬ እጸልያለሁ።

22 አሁንም እጃችንን በእነሱ ላይ መጫናችን፡ ም—ምንኛ ድንቅ ነው… ጌታ ሆይ፡ ይህ ምንኛ ድንቅ ነው፡ እኛ የዚህ ምድር ሰዎች ህጻናት ልጆችን በሰምህ የመባረክ መብት ማግኘታችን፡ ይህም፡ ልመናችንን ሁሉ፡ እንደሚሰጠን፡ ማወቃችን ደስ ይላል። እኛ እነርሱን ለመባረክ ስንነሣ፡ ሁሉን ቻይ፡ በማንም-የማይታየው፡ ኢየሱስ ሆይ እጃችንን በላያቸው ላይ ጭነን ለጌታ አደራ ስንሰጣቸው ጠጋ ብለህ እያንዳንዱን ልጅ ባርክ። በሰሙ እንጠይቃለንና። አሜን።

23 ወንድም ግሌን ፈንክ፡ ለጌታ አደራ የሚሰጡ ሶስት ህጻናት ልጆች ይዟል። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

... በ—በዚያ በሰሜናዊው አገር፡ በሚገኝ ትንሽ ክፍል ውስጥ፡ ይህን ልጅ ቃል ገብተኸልኝ ነበር። አባት ሆይ፡ በረከትህ በእርሱ ላይ ይሁን።

ጆሴፍ፡ ልጄ ሆይ፡ ለእግዚአብሔር አሳልፌ እሰጥሃለሁ። ሕይወትህም በረከት ይሁንልህ። ነቢይ ሁን፡ ጆሴፍ። የእግዚአብሄር ፀጋ ከአንተ ጋር ይሁን። የአባትህ አምላክ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለዘላለም ይባርክህ፡ ሕይወትህ ለሌሎች በረከት እንዲሆን ያድርግ።

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ባረክሁት። አሜን።

24 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] ... ህጻናትን ትወዳላችሁ? እያንዳንዱ እናት ልጇን እንዲባረክላት የምትፈልገው አንዳች ነገር አላቸው።

ዛሬ ጠዋት፡ የሰማዩ አባታችን ለእኛ ለአዋቂዎች ያለው አመለካከትም ይህ ነው። እያንዳንዳችን እንድንባረክለት ይፈልጋል። እነሆ አንድ ነገር አቅርቦልናል፡ አሳልፎ ሰጥቶናል፡ እንዲህ በማለት፡ "እነሆ፡ ልጄ ሆይ፡ እንድትባረክ እፈልጋለሁ።" ድንቅ አይደለምን? ታዲያ እንዲህ ያለውን ደግ ሰማያዊ አባት ልናደንቀው ይገባናል።

25 አሁን፡ ሕፃናት በረከቶች ውስጥ፡ ታውቃላችሁ፡ በቀደም ከቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ በብሉይ ኪዳን፡ አንድ ቦታ ላይ እያነበብኩ ነበር፡ ያን፡ በማንበቤ በ—በእውነት ደስ ብሎኛል። ይኸው፡ እዚህ ጋር አለ። "ናታንም ዳዊትን እንዲህ አለው፡ 'እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነውና፡ በልብህ ያለውን ሁሉ አድርግ።"' እያችሁ? "በልብህ ያለውን ሁሉ አድርግ።" እናንተ ክርስቲያን ወዳጆቼ፡ ብዙ ጊዜ እ—እንዲህ ይገጥመኛል፡ ምን ማለት እንዳለብኝ ሳላውቅ ነገሮችን ተናግሬ፡ ሲፈጸም አየዋለሁ። ያልከው ነገር!

26 በአንድ ወቅት ኢየሱስ ከተራራው ሲወርድ፡ በላይዋ ምንም ያልነበራት ዛፍ እንደገጠመችው ይነገራል፡ ከቅጠል በቀር፡ ምንም ፍሬ ስላልነበራት፡ "ከእንግዲህ ወዲህ ማንም ከአንቺ አይብላ፡" አላት።

27 በማግሥቱ፡ ሐዋርያቱ በዚያ ሲያልፉ፡ ቅጠሎቿ እንደደረቁ አዩ። "ዛፏ በምን ያህል ፍጥነት እንደ ደረቀች እይ፡" አሉት።

28 ኢየሱስም አላቸው፡ "በእግዚአብሔር እመኑ፡ በምትጸልዩበት ጊዜ፡ የፈለጋችሁትን ሁሉ፡ እንደምትቀበሉና እንዳገኛችሁት እመኑ። ምንም ይሁን የምትሉት፡ እና የምትናገሩትን ሁሉ ታገኛላችሁ።" አሰቡት። ኦህ! ምናልባት ዛሬም፡ ታላቁ ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ፡ በመሠዊያው ላይ ቆሞ፡ ትናገራላችሁ... እንግዲህ፡ ያጌጠ መሆን አይጠበቅበትም። በጣም የተራቀቀ ቦታ መሆን የለበትም።

29 ያዕቆብ አንድ ጊዜ ድንጋይ አነሣና ጭንቅላቱን አንተርሶበት ነበር፡ እስከ ዛሬ ድረስ እንደ ሹመት መቀቢያ ድንጋይ ይታወቃል። ወይም፡ የሹመት መቀቢያ ድንጋይ፡ በምድር ላይ ያሉ ታላላቅ ሰዎች አሁንም ይጠቀሙበታል፡ አንድ ማሳ ላይ በተቀመጠ ተራ ድንጋይ ላይ፡ ነገሥታትን አስቀምጠው ይሾሙበት ዘንድ መቀመጫ ይጠቀሙበታል።

ቤቴል በአንድ ላይ የተቀመጡ የድንጋይ ክምር ብቻ ነበረች፡ የእግዚአብሔርም ቤት፡ የመኖሪያ ስፍራ ሆነች። ያዕቆብም፡ “ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት እንጂ ሌላ አይደለም” አለ። አንዱ በአንዱ ላይ የተከመሩ የድንጋዮች ክምር ነበር።

30 በጣም የተጋነኑ ታላላቅ ነገሮች አይጠይቅም። የሚያስፈልገው፡ እምነት እና ነገሮችን ማቅለል ነው። እንዲሆን የሚያደርገው ይህ ነው።

31 አሁን፡ ጊዜው እየሄዴ እንደሆነ፡ እና ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሙቀት እየጨመረ፡ እና እየተጨናነቀ መሆኑን ስላወቅን እናንተን ላለማዘግየት እንሞክራለን። ስለዚህ ዛሬ ጠዋት ለጥቂት ደቂቃዎች ብቻ፡ ይረዳችኋል ብዬ በማምነው በ... በትንሽ ርዕሰ ጉዳይ ላይ እናገራለው። አሁንም፡ ከቤት ከመውጣቴ በፊት፡ ሶስት ወይም አራት ጥቂት ነገሮችን ጻፍኩኝ። “ወደዚያ ስደርስ ጌታ ምን እንድናገር እንደሚፈልግ ለማየት እጠብቃለሁ፡” አልሁ። እዚህ ላይ ስድስት ትናንሽ ነገሮችን፡ ትናንሽ ርዕሰ ጉዳዮችን ጻፍኩኝ፡ አንዱንም ጽፌ፡ በዚህ መልኩ በኪሴ ውስጥ አስቀመጥኩት። “ደህና፡ ወደ መድረክ ስወጣ የምናገረውን ነገር ይሰጠኝ ይሆናል፡” ብዬ አሰብኩ። አሁንም እንዲሁ እዚያው እንደነበርኩ አለሁ። ስለዚህ፡ ለማንኛውም፡ እዚህ ላይ አንድ ጥቅስ አነባለሁ፡ ጌታ እንድንረዳው ይርዳን። ቅዱስ ሉቃስ ምዕራፍ 14፡ ከቁጥር ሰላሳ-... ከሉቃስ 14ኛው ምዕራፍ ከ 31ኛው ቁጥር እንጀምር።

> **ወይም፡ ሌላውን ንጉሥ፡ በጦርነት ሊጋጠም የሚሄድ፡ ከሁለት** እልፍ ጋር **የሚመጣበትን** በአንድ **እልፍ ሊገናኝ የሚችል እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ የማያስብ ንጉሥ ማን ነው?**
>
> **ባይሆንስ፡ ሌላው** ገና... **ሩቅ ሳለ፡ መልክተኞች** ልኮ፡ **ዕርቅ ይለምናል።**
>
> **እንግዲህ እንደዚሁ፡ ማንም ከእናንተ...**

32 በጥሞና ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ። አሁን፡ በመጀመሪያ... ምሳሌ ነው ብሏል። እንዲህ አለ፡ “አሁን፡ ሀያ ሺህ ወታደሮችን ያሰለፈ፡ አንድ ንጉስ እየመጣ ነው፥ **ይህ** አሥር ሺህ ወታደሮች ብቻ ያሉት ንጉሥም፡ ሊገጥመው እየሄደ ነው። ስለዚህ፡ በመጀመሪያ፡ ተቀምጦ ዝግጁ መሆኑን አለመሆኑን፡ መቻሉን አለመቻሉን ይጠይቃል።” መልካም።

> ... **ከእናንተ** ያለውን **ሁሉ የማይተው፡ ደቀ** መዝሙሬ **ሊሆን አይችልም።** (አያችሁ? )

33 ጌታ በዚህ ቃል ላይ በረከቱን ይጨምር። አሁን ለአንድ አፍታ ብቻ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

34 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ አንተ ሁሉን ነገር የምታውቅና፡ የሰውን ፊት የማትመለከት፡ ታሰበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ሰውን የፈጠርከው፡ ልክ እንደ ሜዳ አበባ ነው፡ ዛሬ ቄንጆ ነው፡ ነገ ግን ይቈረጣል፡ ወደ እቶን ይጣላል፡ እሱም ይረግፋል። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬም ምሕረትን እንድታደርግልንና፡ እራሳችንን እንድንፈትሽ እንድታደርገን እጸልያለሁ። እዚህ የምንገኘው እንደ ማረሚያ ቤት ነው። እዚህ ያለነው ለመማር እና እንዴት መኖር እንዳለብን ለማወቅ ነው፡ ዘላለማዊ አምላክ ሆይ፡ ዛሬ ከቃልህ ይውጣ።

ብዙ ልጆችህ ተሰብስበዋል፡ ብዙዎቹም ለዓመታት ልጆችህ ሆነው ቆይተዋል፡ ነገር ግን፡ እንደዚያ፡ ሁላችንም ወደ እግዚአብሔር ቤት ለመማር፡ ለማወቅ፡ ተመልሰን መጥተናል። እኔም፡ ባሪያህ፡ ስለ አንተ የበለጠ ለማወቅ እመኛለሁ። የወንጌልንም መነቃቃት በሁላችን ላይ፡ በባሪያህ ላይ እንድታመጣ እጸልያለሁ፡ መገኘትህም፡ ዛሬም በዚህ ሕንጻ ውስጥ እኛን ማነቃቃትህ፡ በጣም ታላቅ ይሁን፡ በልባችን ውስጥ፡ የተሻሉ አገልጋዮች እንድንሆን በመመኘት፡ እንሄዳለን፡ እዚህ መገኘታችን ለእኛ ማትረፊያችን ነው። መሐሪ አምላክ ሆይ፡ እነዚህን በረከቶች በልጅህ፡ በኢየሱስ ስም ስጠን። አሜን።

35 በምናነበው ቃል ላይ ጌታ በረከቱን ይጨምርልን። በዚህ ጠዋት አንድ ጽሑፍ መውሰድ እፈልጋለው፡ ያም፡ "አባባይ መናፍስት ወይም የእግዚአብሔር ቃል የሚያባብሉ? " አሁን፡ በጣም እንግዳ የሆነ ርዕስ ነው፡ ቢሆንም በዚህ ተበርናክል ውስጥ ስለሆነ… ባለፈውም ረቡዕ ምሽት… ባለፈው እሁድ ጠዋት በ—በትንሽ የወንጌል ኢዮቤልዩ ላይ ተናግሬ ነበር።

36 ባለፈውም ረቡዕ በራሷ ላይ—ድሪም፡ ወይም የሆነ ነገር ስለነበራት ሴት እየሰበክኩ ነበር… አንዲት ሳንቲም ስለጠፋችባት፡ ቤቷንም ጠራርጋ ባለቤቷ ከመምጣቱ በፊት ለማግኘት እየሞከረች ነበር። ይህችም ሴት ምስራቃዊ ዓይነት ሴት መሆኗን፡ እና… ቤተክርስቲያኗን እንደምትወክል ተገነዘብኩ። እና ያኔ የሰርግ ቀለበት የሚለበሰው በጣቱ ላይ አልነበረም። የሚለበሰው በራስ ላይ ሲሆን፡ በውስጡ ዘጠኝ የብር ሳንቲሞች ነበሩት። እናም አንዲት ሴት ሴተኛ አዳሪ ከሆነች፡ አንዱን የብር ሳንቲም ያወጡትና ሴተኛ አዳሪ መሆኗን ያሳያሉ። ስለዚህም ይህች ሴት ሴተኛ አዳሪ አልነበረችም፡ ከሳንቲሞች አንዱ ግን ጠፋባት። ባለቤቷም ሌላ ቦታ ሄዶ ነበር፡ እሷም የጠፋውን ሳንቲም አግኝታ በቦታው ላይ መልሳ ለማስቀመጥ፡ ቸኮለች፡ ምክንያቱም ባለቤቷ ከመጣ ዝሙት ስታደርግ እንደተያዘች ያውቃል፡ ያ ማለት ደግሞ የትዳር መፍረስ እና ሌሎች ነገሮችን ያስከትላል። እኔም ተምሣሌቱን ለአፍታ ያህል፡ ብዙ ታላላቅ ነገሮች ስለ ጠፋባት ቤተ ክርስቲያን ተጠቀምኩበት። አሁንም ጊዜ አባት የሚመጣበት ጊዜ ነው፡ ስለዚህ መፈለግ አለብን። አሁን፡ እንደምናውቀው፡ በቤተ ክርስቲያን እና በተበርናክላችን…

37 ስለ **አባባይ መናፍስት** መናገር እ—እፈልጋለሁ፡ ይህም በእውነቱ **አጋንንታዊነት** የሚል ስያሜ ይኖረዋል። በአሁኑ ጊዜ፡ ስለ አጋንንት ብዙ ትሰማላችሁ፡ ነገር ግን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል የምትሰሙት በጣም ጥቂት ነው። ዲያቢሎስ መኖሩን ሁላችንም እ—እናውቃለን፡ ቁም ነገሩ፡ ግን፡ ያንን እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል ነው። አሁንም… በእግዚአብሔር ጸጋ፡ እነዚህ አጋንንት ከሚባሉት ነገሮች ጋር፡ በየዕለቱ ከመጋፈጥ ጋር ተያይዞ፡ በየቀኑ በዚህ መድረክ ላይ ከእነርሱ ጋር የመግጠም ብዙ አጋጣሚዎች አግኝቻለሁ፡ ስለዚህም፡ ዛሬ ጠዋት፡ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት መመልከት እና እነዚያ ነገሮች ምን እንደሆኑ ማወቅ እፈልጋለሁ።

38 አሁን፡ በፈውስ አገልግሎት፡ ሁልጊዜም በፈውስ በኩል እንተገብረዋለን። ካንሰር፡ እጢ፡ የዓይን ሞራ፡ ሳንባ ነቀርሳ፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ተፈጥሯዊ አይደሉም፡ ከተፈጥሮ በላይ የሆኑና አጋንንት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በግልጽ ያረጋግጣል። ነገር ግን በሰውነት ውስጥ ያሉ አጋንንቶች፡ እንደ ካንሰር ያሉ፡ እድገቶች፡ በውስጣቸው ሕይወት ያላቸው ሲሆን፡ የዚያ ሕይወት ደግሞ

አጋንንት ነው። የዓይን ሞራ እድገት፡ የሳንባ ነቀርሳ ስርጭትና፡ ሌሎች በሽታዎች፡ አጋንንት ናቸው። ያ በአካል መልክ ነው።

39 አሁን፡ ዛሬ ጠዋት ደግሞ አጋንንት በመንፈሳዊ መልክ በነፍስ ውስጥ እንዴት እንደሆኑ እ—እንነጋገራለን። በሰውነት ውስጥ እንዳሉ ሁሉ በነፍስም ውስጥ አሉ። እና በሰዎች አካል ውስጥ እንደምናያቸው አለማመን አንችልም፡ እንደ ካንሰር የመሳሰሉ እና—እና በሰው አካል ውስጥ ያሉ የተለያዩ በሽታዎች ናቸው።

40 ከቅርብ ጊዜ፡ ካንሰር በአራተኛው-አድማስ ውስጥ ያለ በሽታ እንደሆነ ተገልጿል፡ በሌላ አድማስ ውስጥ ያለ በሽታ ነው። እርግጥ፡ አጋንንታዊነት ነው። እያንዳንዱ በሽታ አጀማመሩ፡ የአራተኛው-አድማስ በሽታ ነው።

41 አሁን ግን፡ የሰውነት ውስጥ ወይም የነፍስ ውስጥ ካንሰር ሲሆን፡ አጋንንት በሁለቱም ቦታዎች ላይ ሊመጣ ይችላል። አሁን፡ አብዛኛው ጊዜ ጥሩ አስተሳሰብ ያላቸው ብዙ ሰዎች አሉ... እና እነዚህ መልካም ሰዎች በያዙት ትንንሽ ሥነ መለኮት ላይ ማ—ማረፍ ይፈልጋሉ፡ ወይም ከሕፃንነታቸው ጀምሮ በተማሩት ነገር ላይ፡ በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን አሁንም በውስጣቸው፡ በነፍሳቸው ውስጥ፡ አሁንም ትክክል ያልሆነ ነገር እንዳላቸው ይገነዘባሉ። ብዙዎቻችሁ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ የተገኛችሁ ሰዎች፡ ክርስቲያኖች በሚሰበሰቡበት ስፍራ ሁሉ፡ እነዚህ መናፍስት በውስጣቸው ያሉ ሰዎችን እንደምታገኙ ጥርጥር የለውም፡ ይህም... የሚመኙት ነገር አይደለም። እነርሱ እነዚያን አይፈልጓቸውም። "ኦህ፡ ውሸትን ማቆም ብችል ኖሮ! መመኘትን ማቆም ብችል ኖሮ! **ይህንን** ወይም ***ያንን*** ማቆም ብችል ኖሮ!" ይላሉ፡ እንግዲህ፡ እነዚህ አጋንንቶች ናቸው። አሁንም፡ ብዙ ጊዜ፡ በሃይማኖት መልክ፡ ይመጣሉ። (ሰንደይ ስኩል ስለሆነ፡ የትምህርት ጊዜ ነው፡ እስቲ ይህንን እንመልከት።) ስለዚህ፡ ብዙ ጊዜ፡ በሃይማኖት መልክ ይመጣሉ።

42 እና፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ በአንድ ወቅት፡ ኢዮሣፍጥ የሚባል፡ ታላቅና፡ ሃይማኖተኛ ሰው ነበር። እና የእስራኤል ንጉሥ ወደሆነውም ወደ ሌ—ሌላ ንጉሥም ሄደ። እርሱ ራሱ፡ ኢዮሣፍጥ፡ የይሁዳ ንጉሥ ነበርና። ከዚያም ወደ እስራኤል ንጉሥ፡ ወደ አክዓብ ሄደ፡ አንድ ላይ ተሰባሰበው፡ ራሞት ጊልያድን ለመውጋት፡ እርስ በርሳቸው ተስማሙ። እና አስቀድመው ሳይጸልዩ አደረጉ።

43 አቤት፡ ሰዎች ይህን ቢገነዘቡ! ለዚህም ነው ዛሬ ጠዋት መጥቼ ወደ ውጭ አገር በምሄድበት ጊዜ በጸሎት እንድታስታውሱኝ የጠየቅኋችሁ። በሁሉም ነገር፡ ጸልዩ!

በቀደም አንድ ሰው መጥቶ "ወንድም ብራንሃም፡ እንዲህ እና እንዲያ ማድረግ ስሕተት ነው ብለህ ታስባለህ፡" ብሎ ጠየቀኝ?

44 "ለምን ትጠይቀኛለህ? " አልኩት፡ እያችሁ? በአዕምሯችሁ ውስጥ ጥያቄ ከተፈጠረ፡ ተውት፡ በጭራሽ አታድርጉት። በዚያ ላይ ጽኑ። ማንኛውንም ነገር ማድረግ ከጀመራችሁ፡ ትክክል ወይም ስሕተት መሆን አለመሆኑ ጥያቄ ከሆነባችሁ፡ ከእሱ ራቁ። ስለ ጉዳዩ ጨርሶ አታስቡ፡ ከዚያም ትክክል እንደሆናችሁ ታውቃላችሁ።

45 ስለዚህ፡ ከሁሉ በፊት፡ ነገር ሁሉ በጸሎት ሊታሰብበት ይገባል። "አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ ፈልጉ፡ እነዚህም ነገሮች

ሁሉ ይጨመሩላችኋል።" ዛሬ ጠዋት በትክክል እርግጠኛ ሆኜ፡ ወንዶችና ሴቶች ነፍሳቸው እና፡ አስተሳሰባቸው፡ አመለካከታቸው፡ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም ወደሆነበት ቦታ ቢገቡ ኖሮ፡ ይህች ቤተ ክርስቲያን ከመቼውም ጊዜ ከነበሩት በጣም ኃይለኛ ቤተ ክርስቲያን እንዷ ትሆን ነበር።

46 ለጥቂት ደቂቃዎች ስለ ስጋዊው አካል አስተውሉ። አሁን፡ እኛ፡ ለበርካታ፡ ጊዜያት፡ ለዓመታት፡ "ኤ ላይ ዲተክተር" ብለን የምንጠራው የውሸት ማወቂያ አለን። በጭንቅላታችሁ ላይ ታደርጉትና፡ በ—በእጃችሁ ላይ ታስቀምጡታላችሁ፡ በዚያ ውስጥ ሆናችሁ ውሸትን እውነት ለማስመሰውል ጥረት ማድረግ ትችላላችሁ፡ ሰው እንዲዋሽ ተደርጎ ስላልተፈጠረ፡ ደጋግሞ አሉታዊ ውጤት ይመዘግባል። መዋሸት እታላይነት ነው፡ እጅግ አስቸጋሪ፡ እና ክፉ ነገር ነው። ውሸታም አብሮኝ ከሚኖር፡ ሁሌ፡ ሰካራም ከእኔ ጋር ቢኖር ይሻለኛል። አያችሁ? ውሸታም! ሰውነታችሁ ለውሸት አልተፈጠረም። ምንም ያህል ኃጢአተኛ ብትሆኑም፡ አሁንም የወደቁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። በዛሬው ጊዜ በዚህ ከተማ ውስጥ በጣም ኃጢአተኛ ሰው፡ እግዚአብሔር ኃጢአተኛ እንድትሆኑ አልፈለገም። ወንድ ወይም ሴት ልጆቹ እንድትሆኑ ፈለገ። እናንተ በምሳሌው የተሠራችሁ ናችሁ። ኃጢአት ግን ያንን እንድታደርጉ አባበላችሁ። እና ምንም ያህል ለማስመሰል ውሸትም ትክክል መስሎ እንዲታይ ለማድረግ ብትሞክሩም፡ ስሕተት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሳይንሳዊ መሣሪያ አላቸው። እናንተ የምትፈልጉትን ሁሉ ንጹሕ አስመስላችሁ መናገር ትችላላችሁ፡ አሁንም የሚመዝገብው ግን አሉታዊ ይሆናል፥ ምክንያቱም በሰው ውስጥ ከፊል ንቃተ ሕሊና አለ፡ ይህ ከፊል ንቃተ ሕሊና እውነት ምን እንደሆነ ያውቃል። እዚህ ጋር ምንም ብትናገሩም እንኳ፡ ከፊል ንቃተ ሕሊና ውሸት መሆኑን ያውቃል፡ በከፊል ንቃተ ሕሊና ላይ ይመዘግባል።

47 ስለዚህ፡ አንድ ወንድ ወይም አንዲት ሴት በአሳባቸው፡ በምስክርነታቸው እና በህይወታቸው ሁሉ የመንፈስ ቅዱስ አውታር ከእግዚአብሔር ጋር (አሜን) አንድ እስኪሆን ድረስ በእግዚአብሔር ዘንድ በአንድነት ከተሰለፉ፡ ምን ይሆናል! ወንዱ ወይም ሴቷ በልባቸው ነጻነት፡ በውስጣቸው ጥልቅ እምነት፡ አንድ ለመሆን ከተሰለፉለት!

48 ብዙ ሰዎች እንዲጸለይላቸው ወደ መሠውያው ይመጣሉ፡ እምነታቸው ግን አእምሮአዊ ነው። ኃጢአታቸውን ተናዘው፡ በአዕምሯዊ እምነት ቤተክርስቲያንን ይቀላቀላሉ። በአዕምሯቸው ውስጥ—ያምናሉ። ይህን የሚያምኑት ስለሰሙት ነው። ይህን የሚያምኑት ምርጥ ፖሊሲ መሆኑን ስለሚያውቁ ነው። እግዚአብሔር የሚያየው ግን ይህን አይደለም። እግዚአብሔር አእምሯዊ እምነትን አያይም።

49 እግዚአብሔር የሚመለከተው፡ በልብህ ውስጥ ያለውን ነገር ነው... ከልብ ሲመጣ፡ ያኔ ሁሉም ነገር ይቻላል። ንግግራችሁ እና ሕይወታችሁ አንድ ይሆናሉ። ሕይወታችሁ ንግግራችሁ እንደሚናገረው ጮክ ብሎ ይናገራል።

50 ነገር ግን ንግግራችሁ አንድ ነገር ሲል፡ ሕይወታችሁ ደግሞ ሌላ ነገር ሲኖር፡ የሆነ ችግር አለ ማለት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት በልባችሁ ሳይሆን፡ በአዕምሯችሁ እምነት ስላላችሁ ነው። ይህም የሚያሳየው፡ **እዚህ**፡ በውጭው የእግዚአብሔር እውቀት እንዳለ፡ **እዚህ**፡ በውስጥ ግን፡ የአጋንንት ጥርጣሬ

እንዳለ ነው። “በመለኮታዊ ፈውስ አምናለሁ፡ ግን ለእኔ አይደለም።” አያችሁ? “ኦህ፡ እንደዚህ ሊሆን ይችላል፡ እኔ ግን አላምንም።” ተረድታችኋል? በውጭ፡ “አዎን” ትላላችሁ፣ ውስጥ፡ ህሊናችሁ ግን “አይ” ይላል። ያንኑ ሳይንሳዊው ውጤት ይህ ነገር ትክክል እንዳልሆነ ያረጋግጣል፡ ያረጋግጠዋል።

51 እነዚህ ነገሥታት፡ ከመጀመራቸው በፊት፡ ምን ማድረግ እንደነበረባቸው አስተውሉ... ኢዮሣፍጥ ከአክዓብ ጋር አንድነትን ከመፍጠሩ በፊት፡ እንዲህ ማለት ነበረበት፡ “የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደሆነ ለመጠየቅ እንጸልይ።”

52 ሰባኪም በሉት፡ ክርስቲያንም በሉት፡ የቤት እመቤትም ትሁን፡ ገበሬም በሉት፡ ወይም የፋብሪካ ሠራተኛ ይሁን፡ እግዚአብሔርን በሁሉ ነገር የሚያስቀድም ከሆነ፡ ዲያብሎስ የቻለውን ያህል ሁሉ ቢያድርገውም እንኳ ስኬታማ እንደሚሆን አሳያችኋለሁ። አስቀድሞ፡ እግዚአብሔርን ይሻልና። እኛም በመጀመሪያ...

53 እነርሱ ግን እንዲህ አላደረጉም። አክዓብ ብዙ ነገርን ስላደረገ ታላቅ እና የበለጸገ መንግስት ስለነበረው፡ በዚህ ተጋርዶባቸው ነበር፡ እንዲሁም በባለጸግነት ሁሉ፡ እጅግ የናጠጠ፡ ወርቅና ብር የነበረው፡ እምነት ግን ያልነበረው፡ ታላቅና ስኬታማ ሰው ነበር።

54 ዛሬም ዓለም ያለችበት ሁኔታ ያ ነው። ዛሬ አሜሪካ ያለችበት አቋም ያ ነው። ዛሬ አብያተ ክርስቲያናት ያሉበት ሁኔታ ያ ነው። ከመቼውም ጊዜ ይልቅ የተገነቡ ምርጥ አብያተ ክርስቲያናት ገንብተናል። ከመቼውም ጊዜ የተሻሉ ምሁራን አሉን። ምርጥ የሰነ መለኮት ትምህርት፡ እና የመሳሰሉትን አስተምረናል፡ እንደ መላእክት መዘመርንም ተምረናል፡ የሆነ ቦታ ግን ድክመት አለብን። ድክመት አለ፡ ምክንያቱም ወደ እግዚአብሔር ቃል ከመመለስ ይልቅ፡ የሰው ትምህርትንና አባባይ መናፍስትን ተከትለዋል። ነገሮች እንደ ዓለም ለማሰመሰል ሞከሩ። እንደ ሆሊውድ፡ የሚያብረቀርቁ መብራቶችን ማንጠልጠል ሞከሩ።

55 እዚህ በቀደም፡ በጣም ታዋቂ የሃይማኖት ተቋም፡ መሉ ወንጌል በካንሳስ ሲቲ፡ ወይም፡ ይቅርታ፡ በዴንቨር፡ በነበረው ስብሰባ፡ በሚሊዮን-ዶላር የሚገመት ቤተክርስቲያን በመገንባት ላይ ይገኛል። በሺዎችም የሚቈጠሩ ሚሰዮናውያንም ወንጌልን ወደ አረማውያን ለማድረስ፡ ከዚሁ የሃይማኖት ተቋም አምሳ ሳንቲም ይጠባበቃሉ። ዛሬ የሚያስፈልገን የሚሰዮናዊ-አስተሳሰብ ያለው፡ በእግዚአብሔር-የተላከ፡ በመንፈስ-ቅዱስ-የተወለደ መነቃቃት ነው፡ ይህም ታላላቅና የተዋቡ ቸርቾችን ከመገንባትና፡ ጐረቤቶቹን ለመብለጥ ከመሞከር ይልቅ፡ ጫካ ውስጥ በመግባት፡ ለእግዚአብሔር አንድ ነገር ለማድረግ የእግዚአብሔር ቅንዓት ያደርጋል።

56 በዓለም ላይ ካሉን፡ ታላላቅ ካቴድራሎች ውስጥ፡ተቀምጠን በሰው አስተምህሮዎችና፡ ዶግማዎች ከመጨናነቅ ይልቅ በመንፈስ ቅዱስ ነፃነትና፡ በልባችን ውስጥ እየነደደ ባለው የእግዚአብሔር ፍቅር ባለበት ተልዕኮ ወይም ክፍል ውስጥ ማምለክ እመርጣለሁ። ዛሬ የሚያስፈልገን ወደ እውነት የሚመልስ፡ እንደገና ወደ እግዚአብሔር ቃል የሚመልስ፡ የሚያንቀጠቅጥ ተሃድሶ ነው።

57 እና፡ ወደዚያ ከወረዱ በኋላ፡ ከጊዜ በኋላ ኢዮሣፍጥ ወደ አእምሮው ተመልሶ እንዲህ አለ፡ “እንግዲህ... መልካም፡ እንግዲህ ስለዚህ ጉዳይ

እግዚአብሔርን እናማክረው።"

58 እርሱም አለ፡ "ይሁን፡" አክዓብ እሺ አለ፡ እና በመቶዎች የሚቆጠሩ፡ በጥሩ የሰለጠኑ አራት መቶ ሰባኪዎችን ላከ። ወደዚያም አስመጣቸውና "እነዚህ ሁሉ ትንቢት ተናጋሪዎች ናቸው፡" አለው።

59 እነርሱም ወደ አስማታቸው ገቡ፡ መጣራት ጀመሩ። እነርሱም "አዎን፡ በሰላም ሂድ። እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው፡" አሉት።

60 አራት መቶዎቹ ሰዎች በሙሉ በሰላም እንደሚሄዱ ካረጋገጡ በኋላ፡ አሁንም ኢዮሣፍጥ ግን... ተረድታችኋል? አያችሁ፡ በዚያ በጻድቅ ሰው በልቡ ውስጥ ትክክል ያልሆነ ነገር እንዳለ በወጡ ውስጥ እርጋፊ እንዳለው ተሰማው። የሆነ ችግር ነበር።

61 አክዓብ እንዲህ አለ፡ "አሁን አራት መቶ ሰዎች አመጣን፡ ሁሉም በአንድ ድምፅ፡ ሁሉም በአንድ ላይ 'ሂዱ፡ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ነው፡' ብለውናል አለ።"

ኢዮሣፍጥ ግን፡ "ሌላ አንድ እንኳን የለህም? " አለው

62 እንዲህም አለ፡ "መልካም፡ በአገሪቱ ውስጥ ካሉት የተማሩ ምርጥ አራት መቶ ሰዎች በኋላ፡ አንድ ተጨማሪ ሰው ለምን ያስፈልገናል? ሁሉም 'ሂዱ!' እያሉ ነው" አእምሮአዊ ብልህነት ነበር። ኢዮሣፍጥ ግን በልቡ ውስጥ የሆነ ችግር እንዳለ ያውቅ ነበር። ያም፡ እንዲህ አለ፡ "አንድ ሌላ ሰው አለን፡ ሚክያስ ይባላል። እኔ ግን እጠላዋለሁ።" አለም፡ "ሁልጊዜ ክፉ ነገር ይናገራል፡ ምንም ሥራ በሌለው ጊዜ ይወጣል፡ አብያተ ክርስቲያናትን እና ሁሉንም ነገር ያቃልላል።" "እርሱን አልወደውም፡" አለው።

እርሱም "ሂድና፡ አስመጣው፡ ምን እንደሚል እናያለን፡" አለው።

63 ሚክያስም ሲመጣ፡ እንዲህ አላቸው... እነርሱም "አሁን፡ ይኸውልህ፡ አንተም እንደ ሌሎቹ ተመሳሳይ ነገር መናገር አለብህ፡" አሉት።

64 እርሱም፡ እንዲህ አላቸው፡ "እኔ የምናገረው... " ይኸው ነው። "እግዚአብሔር የሚናገረውን ብቻ እናገራለሁ።" አሜን። "ነብያችሁ ምንም ይበል፡ **ያም** ምንም ይናገር፡ ቤተ ክርስቲያንም ምንም ብትል፡ ሌሎቹ ምንም ይበሉ፡ እኔ እግዚአብሔር ያለውን እላለሁ። እግዚአብሔር በከንፈሮቼ ላይ ያደርጋልና እሱ የሚለውን እላለሁ።" ዛሬ የሚያስፈልጉን እግዚአብሔር ያለውን የሚሉ ተጨማሪ ሚክያሶች ናቸው። ልብ በሉ፡ ስለዚህ አገኙት፡ እርሱም "ዛሬ ማታ ስጡኝ፡" አላቸው። ስለዚህ ጌታ በዚያ ሌሊት ተገናኘው፡ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ተመልሶ መጣ። ሁለቱ ነገሥታት በበሩ ላይ ተቀምጠው ሳሉ፡ "ሂዱ፡" አላቸው። "ሂዱ። ነገር ግን፡" አላቸው፡ "እስራኤል እረኛ እንደሌላቸው በጐች ተበትነው አየሁ፡" አላቸው።

65 ስለዚህ አንደኛው ሰባኪ፡ ሙሉ ልብሱን ለብሶ፡ ቀረበና አፉን መታው፡ እንዲህም አለው፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ ከእኔ ሲወጣ በየት በኩል አልፎ ነው" ብሎ ጠየቀው?

እርሱም "በተመለሰህ ጊዜ ታውቃለህ፡" አለው። አዎን።

66 አለውም፡ "ይኸውልህ አዳምጥ!" "እኛ የእግዜብሔር አገልጋዮች ነን፡ እኛ አራት መቶ ነን፡ አንተም አንድ ነህ፡" አለው።

67 ሚክያስም “ችግርህ ምን እንደሆነ እነግርሃለሁ፡” አለው። አሜን! እንዲህ አለ፡ “ራዕይ አየሁ።” አሜን! እንዲህም አለ፡ “እግዚአብሔር በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ አየሁ። የሰማይ ሠራዊትም በዙሪያው ቆመው አየሁ። እናም ይህ ሰው በሰራው ግፍ ምክንያት፡ በእግዚአብሔር ቃል እንደተረገመ ሁላችንም እናውቃለን።”

68 እግዚአብሔር የረገመውን ልትባርክ አትችልም፡ እግዚአብሔር የባረከውም ዲያብሎስ ሊረግመው አይችልም። ምንም ድሃ ወይም ሞኝ ቢሆን፡ ምንም ያህል ያልተማረ፡ ምንም ያልሰለጠነ ቢሆንም፡ የግል ጉዳይ ነው። እግዚአብሔር የባረከው የተባረከ ነው። እግዚአብሔር የረገመው የተረገመ ነው። መልካሙን ከክፋው ለይታችሁ እወቁ።

69 ሚክያስ በሰባኪዎች ውስጥ የነበረ ጌታ እንዳልሆነ በሚገባ አውቆ ነበር። መልካም፡ የእነዚያ ሰባኪዎች ችግር ምን ነበር? ያደረጉትን አስተውሉ። እነሱ ምርጥ ልብስ ይለብሱ ነበር። የተመረጠውን ምግብ ይመገቡ ነበር። የየራሳቸውን ሥነ መለኮት ብቻ፡ የሚያውቁበት ደረጃ እስኪደርሰ ድረስ፡ በፓርቲዎቻቸውና በመሳሰሉት ውስጥ ተሰባሰበው ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው፡ ሚክያስ ራእዩን በተመለከተ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ “እግዚአብሔርም አለ፡ ‘ወርዶ አክዓብን የሚያታልልን ማን እናገኛለን?’ ውሸታም መንፈስም አለ፡ ‘ወርጄ አክዓብን በእነዚያ ሰባኪዎች አማካኝነት አታልለዋለው፡ የእግዚአብሔር ቃል ይፈጸም ዘንድ፡ አክዓብ ወደዚያ እንዲወርድ አደርገዋለሁ’ አለ።”

70 አሁን፡ በዚህ ሰዓት ብዙ ሰዎች እየሰሙ ይገኛሉ... (አሁን፡ የሰንደይ ስኩል ስለሆነ፡ እወደዋለው።) ተመልከቱ፡ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ከመቀበል ይልቅ አባባይ መናፍስትን እየሰሙ ነው። መናፍስት፡ በዓለም ውስጥ ናቸው። አጋንንት ናቸው። ወደየሰፍራው በመሄድ፡ ከሰዎችና ከአገልጋዮች ጋር ይቀላቀላሉ። በቤተክርስቲያን አባላት መካከል ይገባሉ። በመልካም ሰዎች መካከል ይገኛሉ። እና ቅዠት ውስጥ፡ እንዲገቡ ያደርጓቸዋል። ሰዎቹም፡ የአምላክን ቃል የሚፃረር ነገር ይናገራሉ፡ ያደርጋሉ፡ ያስተምራሉ፡ እንዲሁም ይለማመዳሉ። በዛሬው ጊዜ፡ የቤተክርስቲያንቱ አገልጋዮች በአብዛኞቹ በቤተክርስቲያናት ውስጥ፡ ሰዎች ካርታ እንዲጫወቱ ይፈቅዳሉ። እንግዲህ፡ ካቶሊኮች ብቻ አይደሉም፡ ብዙዎች ፕሮቴስታንቶችም ይህን ያደርጋሉ።

71 ማድረግ የሚሞክሩት ሌላ ነገር ለመተካት። አዳዲስ እቅድ ለማውጣት ይሞክራሉ። የመንፈስ ቅዱስን ቦታ ለመተካት፡ ሰርዓተ ትምህርትን ያለማምዳሉ። ሰዎቻችሁ ምን ያህል የተማሩ ቢሆኑም፡ በጭራሽ ይህንን ማድረግ አትችሉም። ትምህርት ማግኘታቸው ጥሩ ነው ብዬ እሰባለሁ። መንፈስ ቅዱስ ከሌለው ግን፡ ትምህርቱ ምንም አይጠቅምም። ትምህርት የመንፈስ ቅዱስን አመራር ሊተካ አይችልም። አሜን።

72 አስተውሉ፡ እነሱ፡ በዚህ ፋንታ፡ ድሮ በነበረን-ልምምድ ፈንታ የእጅ መጨባበጥን መተካት ዳዳቸው። ዛሬ ቤተክርስቲያኗ ዘመናዊ ሆናለች። የቀኝ እጅ ህብረት ለማድረግ በመስማማት ያገለግላሉ፡ ይህን የሚያደርጉትም በዚህ መንገድ ነው። ይሁን እንጂ ኃጢአተኞች-ወጥተው ከእግዚአብሔር ጋር

እንዲታረቁ የሚያደርጋቸው ጥንታዊውን የቁጭት እንባ አንቢዎችን ሊተካ ፈጽሞ አይችልም። በትክክል።

73 ዛሬ የእግዚአብሔርን አሥራት ለመተካት እየሞከሩ ነው። የሆነ ነገር ለማለማመድ እየሞከሩ ነው። የተለየ ነገር ለማስመሰል እየሞከሩ ነው። ወደ ቤተክርስቲያኖች ሄደው የተለያዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፡ ሎተሪ ይጫወታሉ። ሎተሪ የእግዚአብሔርን አሥራት ፈጽሞ አይተካም። እራት፡ ብርድ ልብስ መሸጥ፡ ሽርሽር፡ የተለያዩ ዕዳዎችን ለመክፈል ገንዘብ ማሰባሰብ፡ የእግዚአብሔርን ዘላለማዊ አሥራት እና መሰዋዕትነት በጭራሽ አይተካም። በጭራሽ አያደርገውም። ሆኖም ለማድረግ እየሞከርን ነው።

74 ይህ ምንድን ነው? የእግዚአብሔርን ቃል በሆነ ነገር ለመተካት፡ የ-... የመጣ አባባይ መናፍስት ነው። እግዚአብሔር ለቃሉ ምትክ የለውም። ዘላለማዊ እና ዘላለማዊ ነው። እግዚአብሔር እምነትን የሚተካበት ነገር የለውም። እምነት ምትክ የለውም። ተሰፋ የእምነትን ቦታ ፈጽሞ አይተካም። እምነት ብቸኛ ነው። ብቻውን ይቆማል። መቼም ቢሆን ተሰፋ የ... የእምነትን ስፍራ አይተካም። ተሰፋ፡ ወይም እምነት ማለቴ ነው፡ ተሰፋ ስለምናደርጋቸው ነገሮች ማረጋገጫ፡ ስለማናያቸው ነገሮች ማረጋገጫ ነው። አያችሁ? ተሰፋ አንድ ነገር ነው፡ እምነት ደግሞ ሌላ ነገር ነው። ተሰፋ ተሰፋን ያደርጋል፡ እምነት ግን ያገኛል። አንደኛው አዕምሮአዊ እምነት ነው፥ ሌላኛው ደግሞ የእግዚአብሔር ቀጥተኛ መገለጥ ነው። በጭራሽ አይተካውም። እኛ እየሞከርን ነው፡ ግን እነዚህን ሁሉ ተተኪዎች እየሠራን ነው።

75 ሚስዮናውያንን ከመላክ ይልቅ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናትን ለመገንባት እየሞከርን ነው። ሌላ ምትክ። ኢየሱስ ቤተክርስቲያን እንዲገነባ ማንንም አላዘዘም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥም አልታዘዘም። ሴሚናሪዎችን አቋቁመናል፡ እነሱም የሚስዮናዊነትን ስፍራ እንዲይተኩ ፈቀዱ። እኛ... ኢየሱስ ሴሚናሪ እንድንገነባ አላዘዘንም። መጥፎ ነገር ባይሆንም። ሰርዓተ ትምህርት፡ ስፍራውን ለመተካት ይሞክራል። በጭራሽ አይችልም። የኢየሱስ ተልዕኮ ለመጨረሻ ዘመን “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ እና ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ፦” ነበር። ስለዚህ ያሉንን ተተኪዎች በሙሉ እውነተኛውን ስፍራ በጭራሽ አይተኩም።

76 በቀደም አንድ የሚተካ፡ አዲስ ልምምድ ገጥሞኛል። ለመጀመሪያ ጊዜ ጥርሴን አሞኝ፡ አንድ ጥርስ ማስወጣት ነበረብኝ። ዛሬ ጥዋት በስፍራው አርቴፊሻል ስክቼበታለሁ። ለማውራት ራሱ ይከብዳል። እውነተኛውን ስፍራ በጭራሽ አይተካም። አይቻልም፡ ዋዳጄ! ኦህ፡ ማይ!

77 አንድን ሰው ወስዳችሁ በደንብ አልብሳችሁ፡ ከእንጨት ፈልፍላችሁ፡ ከኖራ ለስናችሁ፡ የፈለጋችሁት ነገር ብታደርጉት፡ በደንብ ብታስማምሩት። ስሜትም ሆነ፡ ሕሊና የለውም። የእውነተኛ ሰው ስፍራ አይተካም። “የቤተ ክርስቲያን አባል ሆኛለሁ። ከእንግዲህ የተሻለ ነገር ለማድረግ እሞክራለሁ፡” በማለት የሚናገር ሐሰተኛ ሃይማኖተኛም አይሆንም። ከእግዚአብሔር-የተላከውን፡ በመንፈስ-ቅዱስ የተለወጠውን፡ በልቡ-የተለየውን የጥንታዊውን አማኝ ሰው ስፍራ በጭራሽ አይተካምውም። ይህን ማድረግ አይቻልም፡ ምክንያቱም በውስጡ ሕይወት የለም። ሕይወት ሊሰጠው የሚችል ምንም ነገር የለም።

78 እዚህ በቅርብ ጊዜ ይህን የቀረጸ ታላቁን አርቲስት አየሁ፡ ሐውልቱን፡ ማለቴ ነው፡ ይህን የሙሴን ስዕል የሠራው። አሁን ስሙን መጥራት አልችልም። የግሪክ አርቲስት ነው። የሕይወቱን ዋጋ አስከፍሎታል። እናም እሱ በጣም ፍጹም ነው ብሎ ባሰበው ቦታ ላይ በደረሰ ጊዜ፡ በሙሴ ምሰል በጣም ከመደነቁ የተነሳ፡ ጉልበቱን መታውና፡ "ሙሴ ሆይ፡ ተናገር!" አለ፡ በጣም እውነተኛ ይመስላል! እሱ ያሰበውን ሙሴ እስኪመስል ድረስ፡ እጅግ የተዋቀረ ንድፍ ከመሆኑ የተነሳ፡ ስሜት እንዲኖረው ለማድረግ በሞደሻ መታው።

79 በቤተክርስቲያን አእምሮ ውስጥ ተቀምጧል። ምንም ያህል ብትተኩ፡ ምንም ያህል ትልቅ ጉባኤ ቢኖራችሁ፡ ምንም ያህል መዝሙራችሁን ብትዘምሩ፡ ምንም ያህል ጉባኤያችሁ ያማረውን ቢለብሱ፡ ምንም ያህል **ይህን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** ብታገኙ፡ ቢሰማችሁ፡ ብትመቱ፡ ወዘተረፈ። ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ መልክ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን፡ ወርዶ ዳግመኛ የመወለድ አዲስ ተሞክሮ፡ እስኪሰጥ ድረስ የሕይወትን ሰፍራ በጭራሽ አይተካም። የእግዚአብሔርን ቃል ሰፍራ በጭራሽ አይተካም። የእግዚአብሔር ቃል ብቻውን ይጸናል።

80 ሚክያስ ቃሉን ይዞ ነበር። ቃሉ እንዳለው ያውቅ ነበር። ቃሉ በጽሑፍ መልክ፡ እና በራዕይ መልክ ነበረው። እግዚአብሔር በቃሉ የተናገረውን ያውቃል። እግዚአብሔር በራዕዩ የተናገረውን ያውቃል። ሁለቱም አንድ ላይ ተጣመሩለት። እውነት መሆኑን ሰላወቀ፡ በዚህ ምክንያት አልፈራም።

81 ነገር ግን ይህ አባባይ መንፈስ፡ ዛሬ፡ ምን እንዳደረገ ተመልከቱ። የቤተክርስቲያን አባላትን ለማብዛት፡ የቤተክርስቲያን አባላትን ለማዘመን፡ ጥንታዊውን-የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮ ሁሉ እያጠፋ ነው። ሰዎች ካርታ ለመጫወት በሚሰበሰቡበት ምድር ቤት ሰር፡ ማሕበራዊ ግብዣዎች እንዲያደርጉ ይፈቅዱላቸዋል። ቢሆንም መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል የጸለዩበትን፡ ሠገነቱን ፈጽሞ አይተካውም። ሴቶች አንድ ላይ ተሰባሰበው እንዲቀልዱ፡ እና የበሰበሱ እርባና ቢስ ነገሮች እንዲፈጽሙ ያደርጓቸዋል። ቢሆንም የጸሎትን ሰብሰባ ፈጽሞ አይተካም። ሴቶች፡ ዛሬ እየወጡ የሚለብሱት አለባበስ፡ አ—አሳፋሪ ነው።

82 ወንድም ኔቪል ያስቀመጠውን አሳብ ሰምቼዋለሁ፡ እንዲህ አለ፡ "ምስኪኑ የአሜሪካ ሕዝብ፡" "ልብሳቸውን በሙሉ ወደ ውጭ አገር ላክን ይላሉ፡" አለ። ይህ እውነት ነው። በፓንት መዞር ጀምረዋል። ት... ትክክል ነው። ለሚሰዮናውያን መሰጠት አለበት፡ ምክንያቱም ሚሰዮናዊያን... በሌላ አገር ለሚኖሩ ህዝቦችና አረማውያን ያለብሷቸዋል። እነዚህ ሰዎች ያለ እነሱ መቅረታቸው፡ ያንን የወደዱት ይመስላሉ።

83 እላችኋለሁ፡ የሆነ የተዛባ ነገር አለ፡ ይህም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን የወንጌል ሰብከት ነው። ልብሶቻችሁን የሚገፏችሁ አጋንንት ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልብሱን አውልቆ የጣለ አንድ ሰው ብቻ ነበር፡ እርሱም በአጋንንት ተይዞ የነበረው ሰው ነው። ዛሬም የዋህ መሰሎ፡ ማህበራዊ ሆኖ፡ ጥሩ ሰው መሰሎ፡ ሁሉም ደህና አስመስሎ ይመጣል። "ጥሩ የአየሩ ሁኔታ አለ፡ ልብሰሽን ካወለቅሽ ምርጥ ያስመስልሻል።" ወንዶች ግማሽ እርቃናቸውን፡ በግቢ ውስጥ ወደ-ላይና-ታች ይንጎራደዳሉ፡ ሴቶችም እንዲሁ። ለምን፡ እርስ በርሳቸው፡ ውሻ

ከሚያገኘው ክብር በታች እንዲናናቁ ያደርጋቸዋል። ችግሩ ምንድን ነው? እናንተን ለመጉዳት እየሞከርኩ አይደለም። ልነግራችሁ የምሞክረው የአጋንንት ወረራ መሆኑን ብቻ ነው፡ እናንተም "ችግር የለውም፡" የሚሏችሁን አባባይ መናፍስት እየሰማችሁ ነው፡ ግን ውሸት ነው።

84 የሰንዴ ቅንጣት ሰንዴን ብቻ ያፈራል። ክርስቲያን ብትሆኑ፡ እንዲህ አታደርጉም። ይህን ማድረግ አትችሉም። በቃ ይህን አታደርጉም። "ወንድም ብራንሃም፡ እኛ መጽሐፍ ቅዱስን እናምናለን።" የሚል የአዕምሮ እምነት አላችሁ፡ ሕይወታችሁ ግን እንደማታምኑ ይናገራል። አሜን። የእግዚአብሔርን ቃል የሚጠቅሱ አባባይ መናፍስት።

85 ሚክያስ፡ የቆመበትን የሚያውቅ ነበር። የእግዚአብሔር ቃል ነበረው። በጣም ታዋቂ ያልሆነ ሰው ነበር። ምንም እንኳ እነዚያን ሰባኪዎችን ቢወዷቸውም፡ እሱ እውነትን ስለሚናገር ማንም አይወደውም ነበር።

86 በተጨማሪ፡ ሌላ የተፈጸመ ነገር። ከእግዚአብሔር ጋር፡ የግል ልምምድ ያለው ወንድም ይሁን ሴት፡ ትንሽ ስሜታዊ የመሆን አጋጣሚዎች እንዳላቸው አምናለሁ። እንዲሁ እንደሆነ አምናለሁ። ትክክል ነው። ግን ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ፈንታ ስሜታዊነትን ስላዳበሩ ነው። ብዙ ጫጫታዎችን ብቻ ያደርጋሉ፡ በውስጡም ምንም ነገር የለም። በጩኸት እንደምትኖሩ ሁሉ በቅድስናም ኑሩ፡ ከዚያም ደኅና ትሆናላችሁ። ስሜታዊነት ምንም ችግር የለውም፡ "አካላዊ እንቅስቃሴ ማድረግ ግን ብዙም አይጠቅምም።" አባባይ መናፍስቶች ግን በቅድስና ባሉ ሰዎች መካከል ገብተዋል፡ እነርሱም ተቀብለው አርፈውባቸዋል ምክንያቱም "መጮኽ ስለቻሉ" ወይም "መደነስ ስለቻሉ፡ ስሜታዊ መሆን ስለቻሉ ነው።"

87 የእነዚያ የነቢያት፡ የሰባኪዎች ሁሉ፡ አለቃቸው የነበረው ያ ምስኪን ሰው፡ ጥንድ ቀንዶችን ሰርቶ እስኪፋንን ድረስ፡ እስከመደነስ እና ግርግር እስከመፍጠር ድረስ፡ እሱ ትክክል መሆኑን በጣም እርግጠኛ ነበር። የአሦራውያን ሰራዊት ከአገሪቱ ለማባረር ይሄድ ነበርና። ይህ ግን ውሸት ነበር! የእግዚአብሔር ቃል ያለው ሌላ ነውና። አሜን። አያችሁ፡ በስሜት ትክክለኛ መሆን ትችላላችሁ፡ ከጀርባው ትክክለኛ ዓይነት ስሜት ካላችሁ፡ ትክክለኛ ዓይነት ስሜት ስሜታችሁን ያንቀሳቅሰዋል።

88 ዳዊት በጌታ ፊት ሲጨፍር፡ ሚስቱ ሳቀችበት። እግዚአብሔርም ከሰማይ ወደ ታች ተመለከተና፡ "ዳዊት፡ አንተ የልቤ ሰው ነህ፡" አለው። ይሁን እንጂ ዓላማው ትክክል ነበር። በስተጀርባ፡ ህይወቱ ትክክል ነበር።

89 ስለዚህ፡ ስሜታዊ መሆን ስለቻልን፡ ድነናል ማለት አይደለም። ወደ ቤተክርስቲያን እንሄዳለን ማለት፡ ድነናል ማለት አይደለም። እነዚያን አባባይ መናፍስቶችን አትመኑ። እውነተኛ የእግዚአብሔር መንፈስ፡ እውነተኛ የእግዚአብሔር ቃል፡ የእግዚአብሔር እውነት ያ ነው፡ ይህም የእግዚአብሔር ዘር ነው፡ እግዚአብሔርን በሕይወታችሁ ውስጥ ያፈራል፡ እግዚአብሔርን ምስሉ፡ ቅዱሳን፡ ጻድቃን ሁኑ።

90 በብዙ ሰዎች መካከል፡ ሰሜቶችና የመሳሰሉትን፡ ሁሉንም ዓይነት ወሬና ሃሜት፡ እግዚአብሔርን የማያከብሩ ነገሮችን እናገኛለን። ወንድሜ፡ ይህ በቤተክርስቲያኒቱ ውስጥ ሳልፈሪክ አሲድ ነው። የአጋንንት ኃይል ነው። እርስ

በእርስ የሚጋጩ፡ እና ለመገፋፋት የሚሞክሩ የወንዶችና የሴቶች መንፈስ፡ “**ይህ** ትክክል አይደለም፡ **ይህም** ትክክል አይደለም፡ **ያም** ትክክል አይደለም፡” ይላሉ። በደንብ ለመመርመር ከሞከራችሁ፡ እነዚያን ችግሮች ከአስር ዘጠኝ ያህሉን የሚፈጥረው ያ ሰው ራሱ ነው፡ ይህም ልክ አይደለም። አሜን። እግዚአብሔር በወንድማማቾች መካከል አለመግባባትን ይጠላል። ትሁታን ሁኑ፡ ተቀደሱ፡ እግዚአብሔርን ውደዱ፡ ከእርሱ ጐን ቁሙ። ሕይወታችሁ ከመጽሓፍ ቅዱስ ጋር በመጣመር፡ በልብ ንጽሕና፡ በሃሳብ ንጽሕና፡ በወንድማማች መዋደድ፡ የጌታን መንግሥት ለመስራት የተቻላችሁን ጥረት በማድረግ፡ እነዚህን እያደረጋችሁ፡ በትክክል በመልበስ፡ በትክክል በመኖርና እውነት በመናገር፡ ወደ ትክክለኛ ቦታ በመሄድ፡ ሕይወታችሁ ከመጽሓፍ ቅዱስ ጋር እየተጣመረ መሆኑን ካወቃችሁ፡ ከዚያም የፈለጋችሁትን ያህል ስሜት ቢኖራችሁ፡ ሰው ሁሉ ያምናል።

91 ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “እናንተ የምድር ጨው ናችሁ። ጨው ጣዕሙን ቢያጣ፡ ወደ ውጭ ተጥሎ፡ በሰው እግር ከመረገጥ በቀር ለምንም አይጠቅምም።” ጨው ብቻ መሆናችሁ፡ ጥሩ አይደለም። በውስጥ ጣዕም ሲኖራችሁ ግን፡ ጨዋማ ትሆናላችሁ ዓለምም ይጠማል። ጨዋማ ስትሆኑ፡ እነርሱ ይጠማሉ። ኦህ፡ ማይ!

92 አባባይ መናፍስት፡ የሚያታልሉ አጋንንት ወጥተዋል። ይኸውላችሁ፡ ያለነው በመጨረሻው ቀን ላይ ነው። በዘመን ፍጻሜ ላይ ነን። ዓለም አሁን ጫፍ ለመድረስ ተዘጋጅታለች፡ ሊፈርጥ እንደቀረበ መግሉም በቅርብ ቀናት ለመወርወር እንደተዘጋጀ ብጉንጅ ልትፈርጥ ተዘጋጅታለች። ቆሽሻለች። የሚፈውሳት ቅባት የለም። የሚዘንናቸውን––ጠልተውታል። መድኃኒታቸውን ንቀውታል። እያደገ ያለለውን ብጉንጅ፡ የሚያሰቆመውን ፔንሲሊን፡ ወይም ሌላ ነገር ካልወሰዳችሁ፡ እስኪፈነዳ ድረስ ማበጡን ይቀጥላል።

93 ዓለም ያደረገችው ይህንኑ ነው። በቅርብ ጊዜ፡ መንጠባጠብ፡ ጀመረ። እነሱ በጣም ትልቅ ሃሳብ ይዘው ተነሡ፡ የውሸት መናፍስት ወደ ውስጥ ገብተው **ይህንን፡ ያንን**፡ ወይም **ሌላውን** ለሰዎች መናገር ጀመሩ። የተለያየ አመለካከት ያላቸው ዘጠኝ መቶ የሚሆኑ የተለያዩ ሐይማኖታዊ ተቋሞች፡ ሆነን ተከፋፍለናል። “**እስከዚህ** ነጥብ ድረስ፡ እናምናለን! እምነታችን እዚህ ድረስ ነው፡” ይላሉ። መንፈስ ቅዱስ እንዲገባ አይፈቅዱም። የተሻለውን-መንገድ-መከተል አይችሉም። እግዚአብሔር መጮኽ የሚችሉ ብዙ ሰዎች ስላሉት፡ ሁሉም ሰው መጮኽ አለበት። በልሳኖች መናገር የምችሉትን ጥቂቶች ስላሉት፡ ሁሉም ሰው በልሳኖች መናገር አለበት። በአባባይ መናፍስ፡ (ምን? ) በአባባይ ሰዎች መሉ በሙሉ እስኪበከል ድረስ፡ እግዚአብሄር በፍጹም በሌለበት ልዩ ልዩ ስሜታዊነት ለማድረግ ሁሉም የተሸጡ ሆኑ። ከዚያም ወጥተው የፈለጉትን ዓይነት ሕይወት እየኖሩ፡ “ክርስትና፡” ብለው ይጠሩታል።

94 ዓለምም ከማዶ እያያቸው፡ “ኧረ፡ ተመልከቷቸው! ከእነዚህ’ማ እኛም እናንስም፡” ይላል።

95 ባለፈው ማታ ላይ ሰለ አሳማው፡ ሰለ ኃጢአተኛው እንደነገርኳችሁ ነው። ኃጢአተኛ ኃጢአተኛ ነው... መውቀስ አትችሉም። እሱን ለማደሰ አትሞክሩ። **ይህን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** ለመንገር አትሞክሩ። ሲጀመር፡ ኃጢአተኛ

ነው። ሲጀመር፡ አሳማ ነው። ከዚህ የተለየ ነገር አያውቅም። ፊልሞችን ለማየት፡ እና ወደ ኳስ ጨዋታዎችም፡ በእሁድ የሚሄድ ከሆነ፡ እነዚህን ሁሉ ካደረገ፡ ሲጀመር፡ ኃጢአተኛ ነው። ተፈጥሮው እንደ አሳማ ነው። ያረጀ አሳማ አፍንጫውን ወደ ፍግ ክምር አጣብቆ፡ እህል እና ሁሉንም ነገር ይበላል፥ አዎን፡ እንግዲህ፡ አሳማ ነው። እሱን መውቀስ አትችሉም። አሳማ ነው። በቃ ኃጢአተኞች እንዲህ ናቸው። ራስህን ክርስቲያን ነኝ ብለህ የምትጠራ አንተ ሄደህ፡ አብረኸው አፍንጫህን ካጣበቅህ፡ አንተ ራስህ ከሱ አትሻልም፡ እንደውም፡ የከፋህ ነህ። ከመካከልዋ ውጣ። ከዓለም ተላቀቅ። ተላቀቅ። ለእግዚአብሔር ፍቀድለት። ተላቀቅ።

96 እንዴት ትለያለህ? ዛሬ ዛሬ ብዙ ሰዎች፡ “መልካም፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ እንዴት ትላቀቀዋለህ፡” ብለው ይጠይቃሉ? በዚህ ጉዳይ ላይ የ “መላቀቅ፡” ብዙ ሥነ መለኮት እንደሰማችሁ አውቃለሁ። ብዙ ሰዎች እላቀቃለሁ ብለው በማሰብ፡ እስኪያልባቸው ድረስ ይጣጣራሉ። ብዙ ሰዎች መጥተው “የሆነ ነገር ማድረግ እንድችል የአርባ-ቀናት ጾም ጸሎት እገባለሁ፡” ይላሉ። የአርባ-ቀን ጾም አያስፈልጋችሁም። ዓለምንና እነዚህን ሁሉ አጋንንታዊ ነገሮችን ትታችሁ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ልባችሁ ማስገባት አለባችሁ። ይህን እንዴት ማድረግ እንደሚቻል መማር አለባችሁ። ላይ-እና-ታች በመዝለል አትችሉም፡ ወይም ደግሞ በአርባ-ቀን ጾም አታደርጉትም። ይህን ለማድረግ ልባችሁን ለልዑል አምላክ በመማረክ ነው።

97 ልክ እንደ ህጻን ልጅ። ዛሬ ጠዋት፡ ትንሹ ልጄን እናቱ ትንሿ ጃኬቱን ልታደርግለት ስትሞክር፡ እዚያ ጋር አስተዋልኩት። ትንሹን እጁን በጃኬቱ እጀታው ውስጥ ማስገባት ፈለገ። እጁን እዚያ ማስገባት አልቻለም፡ እንዴት ማድረግ እንዳለበት አያውቅም። ትንሹን እጁን መምራት አለባችሁ። እጁን እዚያ ውስጥ ማስገባት ይፈልጋል፡ ነገር ግን በዙሪያው ዝምብሎ እየሞከረ ነው። በጭራሽ ወደ ጃከቱ ውስጥ አልገባም። ጃከቱ ውስጥ አለመሆኑን ታውቆታል።

98 እናንተም ሰታሙ፡ ስትዋሹ፡ እና ሌላው ሁሉ ስታደርጉ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል እንዳልሆናችሁ ታውቃላችሁ። ነፍሳችሁ እስካልተለወጠች ድረስ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል መሆን አትችሉም፡ የቱንም ያህል ቤተክርስቲያን አባል ብትሆኑ፡ ግድ አይሰጠኝም። ወንድሜ፡ አዎን የጥንቱ መንገድ ነው፡ ይህን እንጂ በነፍስህ ውስጥ የሞቀ ሾርባ ያኖርልሃል። በትክክል!

99 እጁን ለማስገባት ሞከረ፡ እጁን እንዴት ማስገባት እንዳለበት፡ የሚመራው ሰው ያስፈልገዋል። ከዚያም እጁን በትንሿ ጃኬቱ ውስጥ ሲያስገባ፡ ደኅና መሆኑን አወቀ።

100 ዳግመኛ የተወለደ ክርስቲያን ሁሉ እንዲህ ነው። በእውነት ወደ እግዚአብሔር ሲገባ፡ ሕይወቱን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያያል ያን ጊዜ የህይወቱ ሁሉ ከሱ ጋር እንደተጣመረ ይገነዘባል። ትዕግሥት፡ ገርነት፡ መረጋጋት፡ የዋህነት፡ ኃይል፡ እምነት፡ ፍቅር፡ ደስታ፡ ሰላም ይኖረዋል። እንደ ተናወጠ ባሕር አይወዛወዝም። ስለ እያንዳንዱ ነገር አይጨነቅም። ንፋስ በበዛበት ውቅያኖስ ላይ እንዳለ ጠርሙስ ክዳን **እዚህ** እና **እዚያ፡** አይዘልም። የተረጋጋ ነው። ልቡ ንጹሕ ነው። ሃሳቡም ንጹሕ ነው። ዓላማውም ንጹሕ ነው። አማራጩም ትክክል ነው። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንደተሰለፈ

ያውቃል። ገሃነም አይቋቋመውም። ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ተሰልፏል። በልቡ ውስጥ፡ ለእያንዳንዱ ወንድና ሴት፡ መለኮታዊ ፍቅርና ንጽሕና አለው። ከ... ከዓለም ነገሮች ተቆጥቧል፡ የዓለም ነገሮች ሞተውበታል፡ ከእንግዲህ አይፈልጋቸውም። ለምን፡ በመንፈስ-ቅዱስ የተሞላች ሴት እምላካዊ-ያልሆኑ ልብሶችን እንድትለብስና በከንቱ እንድትወጣ ማድረግ አትችሉም። አይቻልም፡ ወዳጄ።

101 እንግዲህ፡ እሷን ተሳስተሻል ለማለት መሄድ አያስፈልግም፡ አታምንህምና፡ የምታውቀው ያ ብቻ ነውና። ደስታዋ ያ ነው። ወንዶች ወደቤት በሚመለሱበት ሰዓት፡ አመሻሽ ላይ፡ ጠብቀው ይወጣሉ፡ እነዚያን አይነት ልብሶች ለብሰው፡ ጓሮውን መከርከም እንደፈለጉ መሰለው፡ ወደ ውጭ ይመጣሉ... እስኪ ልክ ከሆነ ንገሩኝ? ሴቶች ሆይ፡ ክፉዎች ናችሁ ለማለት አ—አይደለም። ባለጌ ናችሁ ለማለት አይደለም። ይሁን እንጂ፡ እኅቴ ሆይ፡ እርኩስ መንፈስ እንደያዘሽ አልታወቀሽም። ስለምንስ ታደርጊዋለሽ? ቅዝቃዜ አለመኖሩን የምታውቂበት በቂ ስሜት አለሽ። ሞቃት ነው። ስለዚህ ርኩስ መንፈስ አለ።

102 "እኔ? እኔ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን እሄዳለው፡" ትላላችሁ! ናቡከደነፆርም ታላቅ ሰው ነበር። ግን፡ እብሪተኛ ሆነ፡ እግዚአብሔርም የበሬ መንፈስ ሰጠው፡ ለሰባት ዓመትም ሣር እንዲበላ አደረገው፡ እዚህ አካባቢ እንዳሉ አንድ አንድ ሴቶች ጥፍሩ አደገ። በትክክል። አጋንንትም ያዘው።

103 አንዱም በአጋንንት ተይዞ ልብሱን ገፈፈ። መልሰው ልብስ ሊያለብሱት አልቻሉም። ምን ማለቴ እንደሆነ አያችሁ? አባባይ መናፍስት ነው።

104 ቤተ ክርስቲያናችሁም ይህን ትታገሰዋለች። ሰባኪያችሁ ትንፍሽ እንዳይል ይፈራል፡ ምናልባት እስራታቸውን ባይከፍሉስ ይላል። ምክንያታቸው ይህ ነው። ችግሩ ይኸው ነው። አቤቱ፡ አምላክ ሆይ! ሲጀመር እንዲለወጡና ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቁ ካላደረጋችሁት በስተቀር፡ ለጥምብ አንሳ መንጋ፡ ምን መስበክ ትችላላችሁ? አፍንጫቸውን በሙታን ነገሮች ውስጥ ሰክተው ይውላሉና። የምያስፈልጋችሁ ነገር መጥፎ ነገርን አውጥቶ መጣልና፡ የጥንቱ-መንገድ ሪቫይቫል ከዳር እስከ ዳር ማንቀሳቀስ፡ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክል የሆኑ ወንዶች እና ሴቶችን ማብዛት ነው። ከዓለም ነገሮች፡ ተላቀቁ! ለስለስ-ያለውን ተራ ሰብከት፡ ተውት። አሜን። ወንጌልን ሰበኩ። የተናገረው እግዚአብሔር ነው። "ዓለምን ሆነ፡ በዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮችን ብትወዱ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በውስጣችሁ የለም።"

105 ሰዎች ላይ-እና-ታች መዝለል ይችላሉ፡ ሌሊቱንም ሙሉ ይጮኻሉ፡ በደረቀ የላም ቆዳ ላይ ዐተር እንደመበተን በልሳኖች መናገር ይችላሉ፡ በቀጣዩ ቀን፡ ከቤተክርስቲያኑ ጋር በከባድ መጋዝ ለመዋጋት የሚያስችል ቍጣ ይዘው፡ ማልደው ይወጣሉ፡ ወዲያውኑ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ቤተ ክርስቲያንዋን በሙሉ እንድትፈርስ የሚያደርግ ነገር ይናገራሉ። ዓለም ከሚያባብሉ የአጋንንት መናፍስት በቀር፡ ሌላ ነገር የላትም! ወደ እግዚአብሔር ንጽህና፡ ወደ ቅድስናው፡ ወደ ቃሉ መመለስ እፈልጋለሁ። አሜን። በትክክል። አባባይ መናፍስቶች የእግዚአብሔርን ቃል ይቃወማሉ!

106 አንድ ሰው፡ በቅርብ ጊዜ፡ አንዲት ሴት አመጣ... ካቶሊኮቹ እንደሷ ያሉ ደርዘኖች አሏቸው። መውለድ በምታቆምበት ጊዜ፡ ከእጆቿና ከግንባሯ ላይ

የሚወጣ ነገር ተገኘ አሉ። እንዲህ ያለ ጥሩ የመንፈስ ቅዱስ ሰባኪ... እንዲህ ከሆነ ብዬ አሰብኩ። ሰውዬው የሆነ ነገር በጠርሙስ ይዞ ነበር፡ ከእጀቿ ወሰዶ፡ እየዞረ ሰዎችን ይቀባቸዋል። ዋው፣ አቤቱ ማረን! ፀረ ክርስቶስ ይህ ነው! ደሙ ከአፍንጫዋ ወይም ከራሷ፡ ወይም ከየትዋም ቢወርድ ግድ አይሰጠኝም፡ ወንድሜ፡ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ሊተካ የሚችል ደም የለም። እኔ የማውቀው ብቸኛው ደም ይህ ነው። በአንደኛው እጇ ዘይት፡ በሌላኛው እጇ ወይን እያንጠባጠበች ሊሆን ይችላል፡ ይሁን እንጂ፡ በየትኛውም የሃይማኖት ሥርዓት ውስጥ የምትጠቀሙበት ከሆነ፡ ዲያብሎስ ነው። ሰባኪዎች እንዲህ ላሉ ነገሮች ሲወድቁ ማየት ይደንቃል!

107 የሚያስፈልገን፡ ወደ መሪው መጽሐፍ፡ ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ ነው! ይህ የእግዚአብሔር ቃል፡ የተባረከ የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። “መልካም፡ ወንድም ብራናም ሆይ፡ እንዲህ መሆን የምችል አይመስለኝም። ደስታዬን የማጣው ይመስለኛል፡” ትላላልችሁ። ችግራችሁ ምንድነው? ደስታ ምን እንደሆነ አታውቁም።

108 ሰካራም ወጥቶ ቢሰክር አልኮንነውም ብያችኋለሁ። ለማዳ ነውና። ምንም አያውቅም። ማልዶ፡ ይነሣል፡ ድብርት፡ ሃንጎቨር ይይዘዋል። ወጥቶ ሁለት ወይም ሦስት ጠርሙስ ቢራ ይገዛል፡ ወደ ውጪ ወጥቶም ዊስኪና፡ እንደዚያ ዓይነት ነገሮች ሁሉ ይጠጣል።

ምስኪኑ አጫሽም ወደ ኋላው ተለጥጥቶ፡ እንደ ጭነት ባቡር ሰጋራውን በአፍንጫው ያቦነዋል። በቃ። አልወቅሰውም፡ እርሱ የሚያውቀው ደስታ ያ ነው። የሚያውቀው ያንን ብቻ ነው። በተፈጥሮው፡ አሳማ ነው።

109 የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ራሱ ትልቁ እና ዋነኛው የደስታ ማመንጫ ጣቢያ ሆኖ ሳለ፡ ክርስቲያን ነን እያላችሁ ደስታን ፍለጋ በእነዚያ ነገሮች የምትታመኑ ሁላችሁ ታሳፍራላችሁ። የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል እንደዚያ ላሉ ድብርቶች ላለበት ሰው ምርጥ ማስከሪያ ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ስትጠጡ፡ በመንፈስ ቅዱስ ትሞላላችሁ፡ ያን ጊዜ በቃላት ሊገለጽ በማይችል ደስታና ክብር ተሞልታችሁ፡ አሜን፡ ከዚህ ዓለም እስክትወጡ ድረስ ትሰክራላችሁ። አንድ የማያቋርጥ ማነቃቂያ አለ። ቀን እና ሌሊት የሚያሰክር፡ የማያቋርጥ ስካር! አሜን። እሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።

110 ቤተክርስቲያን ትመጣና፡ ሌላ ነገር ትለማመዳለች። ወደ ባሕር ዳርቻ ወጥተው ትንሽ ፓርቲ በማድረግ፡ መዝናናት ይሉታል። የካርታ ጨዋታ ድግስ በማድረግ፡ ሕብረት። በትክክል። አንዳንዴ፡ አባል ቤት፡ አልፎ አልፎም በቤተክርስቲያኑ ግቢ ውስጥ፡ ጭፈራ ያደርጋሉ። በሆነ ነገር ለመርካት የሆነ ነገር ለማግኘት፡ ጭፈራ፡ ያስለምዳሉ። ምንድነው ችግሩ? እንደው፡ ትልቅ የአሰማ መንጋ ናቸው። ሲጀመር፡ አሳማዎች ናቸው። ከክርስቶስ ጋር ተገናኝተው ቢሆን ኖሮ፡ ደስተኞች ይሆኑ ነበር፡ እነዚያ ነገሮች፡ ከእኩለ ሌሊት ይልቅ ይጠቁሩባቸው ነበር። ወንጌል፡ ሊገለጽ የማይችል ደስታ ክብር የተሞላ፡ በመንፈስ መስከር ነው።

111 ኃጢአተኛን አትኮንኑት፡ ምሕረት አድርጉለት። ተውት ሺሻውን ያጭስ፡ አልኮሉን ይጠጣ፡ የካርታ ጨዋታውም ይጫወት። ደስታው ያ ነው። አትውቀሱት። ደክሞ እና ዝሎ፡ ወደ ቤቱ የሚመጣው፡ ደስታን ፍለጋ

ነው። ከእናንተ የሚጠበቀው ማድረግ ያለባችሁ ነገር ወንጌል ከአሥር ሺህ እጥፍ የሚበልጥ ነገር እንዳለው፡ ልታረጋግጡለት የምትችሉበትን አምላካዊ ሕይወት መኖር ነው። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ አለ—አርታዒ።] በአልኮል መጠጥ፡ በዚህ ሁኔታ ከሞተ፡ ወደ ሲኦል ይሄዳል። ይህ የዲያብሎስ ሰካር ነው። ያንን አሮጌ ሺሻ እየሳበ፡ ከሞተ፡ ፈራጃቸው እግዚአብሔር ነው። ወደ ውጪ ወጥቶ፡ ሲጨፍር፡ ሥነ ምግባር የጐደለው ልብስ ለብሶ ሲዘዋወር፡ እዚያ ከሞተ፡ ፈራጃቸው እግዚአብሔር ነው።

112 አንድ ነገር ግን አለ፡ እንደ እስጢፋኖስ በቅዱስ መንፈስ ቅባት ኃይል ሥር ከሞትክ ግን፡ እርሱ ቀና ብሎ የእግዚአብሔርን ፊት ተመለከተና፡ "ሰማይ ተከፍቶ፡ ኢየሱስም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ፡" አለ፡ ስለዚህ ጎጃው እንደማይጠፋበት እንደ ማርቲን፡ የሰማይ ወገን ናችሁ። አሜን።

113 አባባይ መናፍስቶች የእግዚአብሔርን ቃል ይቃረናሉ! ተውት፡ ተላቀቁ። "እንዴት ይቻላል፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ? " በቃ ተዉት። ማድረግ ያለባችሁ ይህ ብቻ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ተቀበሉ። በራሳችሁ ምንም አትሞክሩ። መሠዊያው ላይ ወርደህ አትደብድበው፡ እየተንከባለልክ "እግዚአብሔር ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስን ስጠኝ! ጌታ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስን ስጠኝ፡" አትበል! መሠዊያን በመደብደብህ፡ አይመጣም። ይህ ምንም ጥቅም የለውም። በጭራሽ። የሚመጣበት መንገድ ይህ አይደለም። እርሱን፡ እንደ ቃሉ በማመን ነው!

114 ጰጥሮስን ተመልከቱት። ጴጥሮስ ችግር ውስጥ ገባ፡ የሚሞት መስሎት ነበር። ከዛ በኋላ ጌታ በውኃ ላይ እየተራመደ፡ ሲመጣ እየ። እርሱም "ጌታ ሆይ፡ አንተ ከሆንክ፡ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ፡" አለው።

ጌታም "ና፡" አለው።

115 እና ጴጥሮስ እንዲህ ብሏልን፡ "እስኪ አንድ ደቂቃ ቆይ፡ ጌታ ሆይ፡ በዚያ ውኃ ላይ መራመድ እችል እንደሆነ፡ ወይም እንዳልሆነ ለማየት፡ አርባ-ቀን ጾም እጾማለሁ። ጌታ ሆይ፡ በቂ መንፈስ ሙላኝ፡ በዚህ ታንኳ ውስጥ፡ በመንፈስ መደነስ እና በልሳኖች መናገር እችል ዘንድ እርዳኝ፡ ያን ጊዜ እወጣለሁ" አለን? አላለም፡ ጌታዬ! እግዚአብሔርን በቃሉ አምኖ ተቀበለ፡ ለቀቅለት እና ተወለት። ያን ጊዜ እግዚአብሔር አሳለፈው።

116 እግዚአብሔር ከሙሴ ጋር ተገናኝቶ፡ "ሙሴ፡ ወደ ግብጽ ወርደህ፡ ለፈርዖን፡ 'ሕዝቤን ልቀቅ' ብለህ ንገረው" ቢለውስ? ሙሴም እንዲህ ቢል፡ "አምላክ ሆይ፡ አስቀድሜ አንተን ለመታዘዝ የሚያስችል እምነት ይኖረኝ እንደሆነ ለማየት፡ አርባ-ቀን፡ እጾማለሁ። አንድ ነገር ስጠኝ፡ ሌላ ነገር ስጠኝ፡ ጌታ ሆይ። ይኸውልህ፡ በመጀመሪያ፡ በመንፈስ መሆን ከቻልኩ ልመልከት" ቢለው ምን ይደረግ ነበር? ሙሴ ምንም ጥያቄ አልጠየቀም፡ እግዚአብሔርን በቃሉ አመነና፡ ሄደ። ይህን ማድረግ ያለባችሁ በዚህ መንገድ ነው፡ እግዚአብሔርን በቃሉ ላይ ውሰዱ። ከዚያም ማድረግ እንደምትችሉ ታውቃላችሁ። እሱ ሌላ ነገር እስኪሆን ድረስ አልጠበቀም፡ ሄደና አደረገ።

117 ኤልያስስ፡ በቀርሜሎስ ተራራ፡ ለረጅም ጊዜ ከቆዬ በኋላ ሲወርድ ምን ሆነ? ከዚያም አንድ ደሃ መበለት ሴት አገኘ። እሷ... እሷም መጻተኛ ነበረች፡ አህዛብ ነበረች። ባገኛት ጊዜ፡ ከጓሮች፡ አንዳንድ እንጨቶችን እየለቀመች ነበር።

እግዚአብሔርም “ወደዚያች መበለት ቤት ውረድ፡” አለው። ሰባኪው እንዴት ወዳለው ቦታ ሄደ!

118 ወደ መበለቲቱ ቤት ወረደ። ስትለቅምም፡ ሁለት እንጨቶች አገኛት። “ምን እያደረግሽ ነው፡” አላት?

119 እንዲህ አለችው፡ “ሁለት የበቆሎ እንጎቻዎች ለመሥራት የሚበቃ ብቻ አለኝና። ጥቂት እንጨቶችን እየለቀምኩ ነው። የቀረኝ ይህ ብቻ ነው። ዝናብ ከዘነበ ሦስት ዓመት ሆኖናል” አለችው። “እነሆ እነዚህን የበቆሎ እንጎቻዎች አዘጋጃለሁ። እኔ እና ልጄ እንበላለን፡ ከዚያም እንሞታለን፡” አለችው።

120 እንዲህ አላት፡ “አስቀድመሽ፡ ለእኔ አዘጋጂልኝ!” ሃሌሉያ! ኦ፡ ትንሽ ወፈፌ እንደሆንኩብሽ አውቃለሁ፡ ለማንኛውም፡ ከጌታ ዘንድ ነኝና። “የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡ አስቀድመሽ፡ ለእኔ፡ አዘጋጂልኝ።” ይላልና። ይኸው እንግዲህ።

121 ምንድነው? “አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ ፈልጉ።” የእግዚአብሔር መንግሥት ሲደመር “ትንሽ ጫጫታ” አይደለም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሲደመር “ትንሽ ስሜት” አይደለም፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሲደመር “ትንሽ **ይህ** ወይም **ያ**” አይደለም። ይሁን እንጂ፡ “እግዚአብሔርን፡ እና ጽድቁን፡ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል።” እግዚአብሔርን አስቀድሙ!

122 አሁን፡ ያቺ መበለት ሰማች። “እምነት የሚመጣው በመስማት ነው፡ መስማት ደግሞ በቃሉ አማካኝነት ነው።” እሷም፡ “ይህ ሰው የእግዚአብሔር ቅዱስ ሰው ነውና፡ ይህም የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሰውዬው የእግዚአብሔር ነቢይ ነው፡ እውነት መሆኑን አውቃለሁ። ይህ የእግዚአብሔር ቃል ነው” አለች።

123 አሁን፡ እንዴት ማድረግ እንዳለባት ለመጠየቅ ወደ ጎረቤት አልሮጠችም። ወደ ጎረቤቶቿ ሄዳ ማማከር... ጎረቤቶቿን መናገር አልፈለገችም፡ “እሺ፡ ምን ታስባላችሁ? ወደ ቤቴ የገባው ሰባኪ፡ **እንዲህ** እያለ ነው። ሱዚ፡ **በዚህ** ላይ ምን ታስቢያለሽ? ” አላለችም፡

124 ወደ ውስጥ ገባች፡ ያላትን መጨረስ ጀመረች። ለቀቀችው። የበለጠ ለማግኘት፡ ያላት ነገር ሁሉ ተወች። በዛሬው ጊዜ ዓለም የሚያስፈልገው ይህንኑ ነው፡ ያላችሁትን ሁሉ-የመልቀቅ ጥሩ-ልምድ ነው። ሃሌሉያ! ጨረሰች፡ ስለዚህ ልትሞላ ነው። የነበራትን ዘይት ሁሉ፡ የነበራትን ዘይት ሁሉና የነበራትን ምግብ ሁሉ፡ ለሰባኪው፡ ለእግዚአብሔር መንግሥት ሰጠች። ያላትን ሁሉ ካራገፈች በኋላ፡ እግዚአብሔር መጣ፡ የምግብ በርሜሉን ሞላ፡ የዘይት ማሰሮውን ሞላ። እሷም እንደገና፡ በሰባኪው ሳህን ላይ አኖረችው። ይመጣል፡ እንደገና ይሞላል። ወደ ውስጥ ይሞላል። በጨረሰች ቁጥር፡ እሱ ይሞላል።

125 እኔ ዛሬ፡ እላችኋለሁ፡ ሰው ይህን ሁሉ የማይረባ ነገርና፡ የማስመሰል ክርስትናን ቢጥልና፡ መንፈስ ቅዱስ ቦታውን እንዲተካ ቢፈቅድ፡ በኤይዝ ኤንድ ፔን ጐዳና ላይ ሪቫይቫል ይጀምራል ይህም መላውን አገር ይሸፍናል። የማይረባ ነገር አቁሙ። ወደ እግዚአብሔር ቃል ተመለሱ። መሞላት እንድትችሉ፡ ጣሉት። እናንተ ልቀቁት፡ እግዚአብሔርም ይመጣል። እናንተ ትጨርሳላችሁ፡ እግዚአብሔርም ይሞላል። እነዚህን ጥቃቅን፡ ነገሮችን፡ “**ይህን** ማድረግ አለብህ፡ **ያንን** ማድረግ አለብህ፥ **ይሄን** ማድረግ አለብህ **ያንን** ማድረግ አለብህ።” እርሱት! ከነፍሳችሁ አስወግዱት!

126 እንዲህ በሉ፡ “አምላክ ሆይ፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ፡ ሙሉ በሙሉ የ... የአንተ፡ እንድሆን ፍቀድልኝ። ጌታ ሆይ፡ የተሰበረ ልብ ይዤ መጥቻለሁ። የተዋረደ መንፈስ ይዤ መጥቻለሁ። እወድሃለሁ። እንደምወድህ ታውቃለህ። እናም እነዚህን ሁሉ ሞኝነት የአርባ-ቀን ጾም እና ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እችል እንደሆነ ማየት እፈልጋለሁ የምለውን ነገር፡ **ይህንን፡ ያንን** ሁሉ፡ **ሌላውን**፡ ይህን ሁሉ የማይረባ ነገር መርሳት እፈልጋለው።”

127 አቁሙት! በቃሉ ውስጥ አርባ-ቀን ጹሙ የሚላችሁ ምንም ነገር የለም። ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር ካላላችሁ በቀር፡ እንድትጾሙ የሚነግራችሁ ምንም ነገር የለም። እግዚአብሔር ነግሯችሁ ከጾማችሁ፡ አይርባችሁም፡ ይሄ ሁሉ አይሆንም። ወንድሜ ሆይ፡ ስትጾሙ፡ ሁል ጊዜ ደስታና ሐሴት ታገኛለህ። እንዲህ አለ፡ “ግብዞች እንደሚያደርጉት፡ ረዥምና፡ አሳዛኝ ፊት ይዘህ ለሰዎች አትታይ። ‘አርባ-ቀን ጾም ላይ ነኝ። ከእንግዲህ ሳህኖቼ አይመጥኑኝም። ሠላሳ ፓውንድ ቀነስኩ፡ ይህም ካለቀ በኋላ ቆንጆ ሆነሻል አሉኝ።’” ኦህ፡ ከንቱነት! የዲያብሎስ አባባይ መናፍስት ነው።

128 ወደ መሠዊያው ተነሥታችሁ፡ መናገር እስኪያቅታችሁ ድረስ “ክብር፡ ክብር፡ ክብር” ትላላችሁ፡ “መንፈስ ቅዱስን ከመቀበላችሁ በፊት በልሳኖች ተናገሩ፡” ትላላችሁ። ከንቱነት! አወጥታችሁ ጣሉ!

129 ይህን ከስርዓታችሁ አውጡና ወደ እግዚአብሔር ቃል ኑ! እርሱም፡ “ንስሓ ግቡ፡ እያንዳንዳችሁም፡ ለኃጢአታችሁ ስርየት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ” አላቸው። እግዚአብሔር ቃሉን ካልጠበቀ፡ እርሱ አምላክ አይደለም። አሜን። አውጥታችሁ ጣሉት። ተሞሉ። አሜን። ዋው! ደስ አለኝ። ያ ቃሉ ነው። እግዚአብሔር ብሏልና። ትክክል ነው። እግዚአብሔር ሲናገር፡ እግዚአብሔር ይፈጽመዋል። በጣም ጥሩ። የምታደርጉት ዝግጅት ሁሉ፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ የምትችሉት ነገር ሁሉ...

130 ይህ ማለት ልክ እዚህ ብዙ የጭነት መኪኖችን በሚሰሩበት የመኪና ፋብሪካ ውስጥ፡ ወይም፡ ብዙ የመንገደኞች መኪኖችን የሚሠሩበት ቦታ አለ። እዚያ እሠራ ነበር። እነርሱም ትላልቅ ፋርጎዎችን ሁሉንም ነገር ይሰራሉ፡ ጠንካራም እንጨት ነገር በውስጡ ያስቀምጣሉ፡ በዙሪያው ማሃጎኒ የሚባለውን ይጨምራሉ፡ ሁሉም ነገር በጣም ቈንጆ ነው፡ ከዚያ ትራኩ ላይ ያስቀምጡታል፡ ግን ምንም እንቅስቃሴ የሌለው የሞተ ነው። በዚያም ሞተር ይደረግበታል፡ የሚያንቀሳቅሰው ሃይል ግን የለም። ዝም ብሎ ይቀመጣል።

131 ዛሬ የሚያስፈልገው የቦይለር ውስጥ እሳት ነው። ዛሬ የሚያስፈልገን የሚያንቀሳቅሰን ሃይል ነው። በዛሬው ጊዜ፡ ቤተክርስቲያንቷ፡ እንድትፈላ የሚያስፈልጋት፡ ኃጢአትን ከህይወታችሁ ለማስወገድ የሚያስችላት፡ የሚፈላ ፍቅር ነው። እርስ በርሳችሁ የማትዋደዱ ከሆነ፡ ያላያችሁትን እግዚአብሔርን እንዴት ልትወዱት ትችላላችሁ? ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናል። ከእግዚአብሔር ጋር ፍቅር ይኑራችሁ፡ ከዚያም እርስ በርሳችሁ ትዋደዳላችሁ፡ ከዚያም ቤተ ክርስቲያንን ትወዳላችሁ፡ ዓላማውን ትወዳላችሁ፡ የእግዚአብሄር የሆነውን ነገር ሁሉ ትወዳላችሁ፡ እንዲሁም ከዓለም ነገሮች ርቃችሁ ትኖራላችሁ።

132 ሰዎች **ይህንን፡ ያንን፡ ሌላም** ማድረግ አለባቸው እያሉ አባባይ መናፍስቶች በየቦታው ይዞራሉ፡ "**ይህን** ማድረግ አለባቸው። **ያንን** ማድረግ አለባቸው።" ይህ የሆነበት ምክንያት የሃይማኖት ተቋሞች፡ ትንሽ መገለጥ ቢጤ ይዘው እየወጡ እንዲህ ስለሚሉ ነው፡- "መልካም፡ አሁን፡ ሰው እንዲህ ማድረግ አለበት ብለን እናምናለን... በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመጮኽ እምናለሁ።" ትክክል ነው። ያ እውነት ነው። ከዚህ ተነስተው የሐይማኖት ተቋም ይመሰርታሉ፡ "ከጮህክ፡ ያን ጊዜ ተሞልተሃል" ይላሉ። ነገር ግን አልተሞላህም።

133 ሌላውም ይነሣና፡ "በልሳኖች መናገር ነው፡" ይላል። ትክክል ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው። "መልካም፡ በልሳን ከተናገርክ፡ ተሞልተሃል።" ብዙዎች በልሳኖች ተናግረው ያልተሞሉ ግን አሉ። አያችሁ? ያ አይደለም። አይደለም፡ ወዳጄ።

ብዙዎቹ፡ "መልካም፡ ትንቢት መናገር አለብን" ይላሉ።

134 እነዚህ በራሳቸው ላይ ቀንዶችን ተክለው የሚተነብዩ፡ ላይ-እና-ታች የሚዘሉ ነብያቶች ተመልከቷቸው። ሚክያስም፡ "እናንተ፡ ሁላችሁም፡ ውሸታሞች ናችሁ" አላቸው። አሜን። በትክክል። እግዚአብሔር እንደዚህ አይመጣም። እግዚአብሔር የሚመጣው በንስሐና በተሰበረ መንፈስ ወደሚመጣው፡ ወደ ቅን ልብ ነው። "በእንባ የሚዘራ፡ የከበረ ነዶ ይዞ፡ በደስታ ተመልሶ እንደሚመጣ፡ ጥርጥር የለውም።" አሜን። በትክክል ተረዳው፡ ወዳጄ።

135 ብዙ አጋንንቶች፡ በሰው ነፍስ ውስጥ የሚሰሩ መናፍስት! ፍሬውን የት እንደሚያፈራ እዩት። ሰው ምን ዓይነት ሕይወት እንደሚኖር ተመልከቱ። እንቅስቃሴአቸውን ተመልከቱ፡ አደራረጋቸውን ተመልከቱ፡ ዓላማቸው ምን እንደሆነ ተመልከቱ። ማይቻል ነው... እንደዚህ ብላችሁ፡ "እነዚህ መኪኖች፡ ሁሉም በሰልፍ እዚህ ተቀምጠዋል... ገነት በቻርልስታውን ናት። መግቢያውም ይህ ነው። በእግር አይቻልም። ብቸኛው መግቢያ፡ በመኪና ነው። መስመሯንም የሚያልፍ ማንም ሰው አምስት ጋሎን ቤንዚን ማምጣት አለበት" ብላችሁ። መኪናው አለ፡ ቤንዚን ከሌለው ግን መንዳት አይችልም። እንግዲህ፡ የሰማያትም መንገድ፡ በትክክል እንደዚህ ነው። እንዴት እንደኖራችሁ እና ስንት መኪናዎች እንዳላችሁ ግድ አይሰጠኝም፡ እግዚአብሔር ሳይኖራችሁ ከሞታችሁ፡ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚጎትታችሁ የእግዚአብሔር ፍቅር ከሌለ፡ ጠፍታችኋል።

136 ነጌቲቭ እና ፖዘቲቭ አለ። ይህ ሽቦ የቱንም ያህል ፖዘቲቭ ፍሰት ቢኖረውም፡ ግራውንድ ሽቦ ከሌለው፡ በጭራሽ አያበራም። በትክክል። እናንተም በእግዚአብሔር ፍቅር ሥር ሰዳችሁ፡ የተመሰረታችሁ መሆን አለባችሁ። ኦህ፡ ወንድሜ ሆይ! ነጌቲቩን እና ፖዘቲቩን አንድ ላይ አምጣቸው፡ ብርሃን ይበራልሃል፡ ጥሩውን የጥንት-ወንጌል ብርሃን ታገኛለህ። ከባሕር ዳርቻ እስከ ዳርቻ እንዲሰራጭ አድርጉት። ያለሱ በጭራሽ አትሞሉም። ፖዘቲቩን ጋር ብቻ የቱንም ያህል ብትዘሉ እና ብትፈርጡ፡ ብርሃኑን ለማብራት ግራውንድ ሽቦ ሊኖራችሁ ይገባል። አሜን።

137 አስተውላችኋል? የግራውንድ ሸቦ እዚህ ጋር እንዲህ ታዘጋጃላችሁ፡ እያንዳንዱም ፍሰትም ወደ ማከፋፈያው፡ ወደ ግራውንዱ ይወርዳል። አንድም ሰው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ሥር የሰደደና የተመሰረተ በሚሆንበት ጊዜ፡ የወንጌሉን ብርሃን ለማብራት፡ መልሕቁን፡ የእግዚአብሔር ማሰሪያ ምሰሶ ወዳለበት ወሰዶ፡ በቀራንዮ ላይ፡ ሥር የሰደደና የተመሰረተ ያደርገዋል። አሜን።

138 ችግሩ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሰዎች በእነዚህ ታላላቅ የቀዘቀዙ መደበኛ የመቃብር ሰፍራዎች ውስጥ፡ ወንጌልን እንደሚሰብኩ ያስመስላሉ። አንድ ምስኪን ሰባኪ ትናንት ወደ እኔ መጣ፡ በአሁኑ ጊዜ በምድሪቱ ውስጥ ካሉት ከካቶሊክ ውጭ፡ ካሉ ታላላቅ የሃይማኖት ተቋሞች ውስጥ የአንዱ አባል ነው። "ወንድም ብራንሃም፡ ደክሞኛልም አሞኛልም፡" አለኝ። እንዲህ አለኝ፡ "ሁላችንም ሰባኪዎች ካባ እንድንለብስና ኮሌታችንን እንድናዞር፡ የ— የተወሰኑ ነገሮችን እንድንሰብክ ሊያደርጉን ነው። በሩብ ሰዓት፡ ምን መሰበክ እንዳለብን ይነግሩናል" አለኝ። "ከእንግዲህ ልቋቋመው አልችልም፡" አለኝ። "ምን ማድረግ አለብኝ? ወንጌልን መሰበክ መጀመር አለብኝ ወይ፡" ብሎ ጠየቀኝ?

139 እኔም፡ "ወንድሜ፡ ከሃይማኖት ተቋሙ ጋር እስካለ ድረስ፡ አክብረው። የሚሉህን ብቻ ተናገር። ነገር ግን ወደ ቄሳችሁ ወይም ወደ በላይ ተቆጣጣሪ ሂድና፡ እንዲህ በላቸው፡ 'ጌታዬ፡ እኔ በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ ተወልጃለው። የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው። ይህን እንድሰብክ ከፈቀዳችሁ፡ በቤተክርስቲያናችሁ እቆያለሁ። ካልፈቀዳችሁ ግን፡ እሄዳለሁ። ሌላ ሰው አስረክቡት።'" መደረግ ያለበት በዚህ መንገድ ነው። ዳር ዳሩን አትዙር። ነጌቲቭ አትሁን። ውጣና እውነቱን ተናገር። በትክክል።

140 እርሱም እንዲህ አለ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ ጉባኤ ይኖረኛል ብለህ ታስባለህ? "

141 "ሰጋ በወደቀበት፡ ንሰሮች ይሰበሰባሉ፡" አልኩት። ትክክል ነው፡ ይከተሉሃል።

142 አንድ ጊዜ፡ ጫጩቶችን እንደፈለፈለው፡ ሰውዬ። አሁን፡ ቀልድ አይደለም። ለመቀለድ አይደለም። ነጥብ ለማስቀመጥ ነው። ዶሮውን ማስታቀፍ ፈለገ፡ እና በቂ እንቁላል አልነበረውም። እና ከአንዷ ስር የዳክዬ እንቁላል አስቀመጠ። ሁሉም ተፈልፍለው ሲወጡ፡ ዳክዬው ዶሮዎቹ አይተውት የማያውቁት ልዩ-መልክ ያለው ነበረ። ዶሮዋ ጭጩቶቿን ኑ ስትላቸው ጫጩቶቹ ይመጣሉ፡ ዳክዬው ግን ቋንቋውን አያውቅም። አንድ ቀን፡ ግን፡ ዶሮዋ ወደ ጓሮ አወጣቻቸው። ከጓሮው በስተጀርባ አንድ ምንጭ ነበር። ይህ ትንሽ ዳክዬ ውኃውን ሲሸተው፡ በኃይል ዘሎ በፍጥነት ወደ ውኃው ገባ። ዶሮዋም፡ "ክላክ፡ ክላክ፡ ክላክ" አለች። ትንሹ ዳክዬም፡ "ሆንክ፡ ሆንክ፡ ሆንክ" አለ። ወደ ውኃው ሮጠ። ለምን? በተፈጥሮው፡ ዳክዬ ነው። ወንድሜ፡ ውሃውን ሲሸተው፡ መራቅ አልቻለም፡ ምክንያቱም ዳክዬ ስለሆነ።

143 ዛሬም እላለሁ፡ እግዚአብሔርን በእውነት ማግኘት የሚፈልግ ማንም ሰው፡ መኖር የማይቻላቸውን፡ **ያንን** ወይም **ሌላውን** እንዲኖሩት ቤተክርስቲያን እንድትነግራቸው አይፈቅዱላትም። የእግዚአብሔር ተፈጥሮ በውስጣችሁ ካለ፡ ወደ ቅድስና ትሄዳላችሁ። ወደ ትክክለኛው መንገድ ትሄዳላችሁ።

ለትክክለኛው ነገር ትቆማላችሁ። ትክክለኛውን ነገር ታደርጋላችሁ። ትክክለኛውን ነገር ታስባላችሁ። ትክክለኛውን ነገር ትኖራላችሁ። ዳክዬ ከሆናችሁ፡ ውኃን ትወዳላችሁ። ክርስቲያን ከሆናችሁ፡ ክርስቶስን ትወዳላችሁ። ዲያቢሎስ ከሆናችሁ፡ የዲያቢሎስን ነገር ትወዳላችሁ። ጥምብ አንሳ ከሆናችሁ፡ ደግሞ የሞተ ነገር ትበላላችሁ። አሳማ ከሆናችሁ፡ ብስባሽ ትበላላችሁ። ዛሬ የት ናችሁ? በትክክል። የጌታን ነገር እየበላችሁ፡ እዚህ ላይ እንደሆናችሁ ታስባላችሁ፡ ከዚያም ከዲያብሎስ ጋር ለመተባበር ትወርዳላችሁ። የሆነ ችግር አለ። እነዚህን መናፍስት መስማት አቁሙ፡ አጋንንት ናቸው። ብቻችሁን ብትቆሙ እንኳን ችግር የለም። በነገሮች በፍጹም የማይወሰዱ፡ ወንዶች እና ሴቶች፡ ከእግዚአብሔር ጋር ብቻቸውን የጸኑ ወንዶች እና ሴቶች ነበሩ።

144 ሚክያስ፡ እንዴት እንደጸና ተመልከቱ፡ እንደ የጂብራልታር ዓለት አይደለም፡ እንደ ዘመናት ዓለት እንጂ። እርሱም፡ "ሴሚናሪው ምን አለ አያገባኝም... እኔ ሌላ ነገር አልናገርም። የጉባኤዬ አባላትም ምንም ቢሉ አይገደኝም። ንጉሡ ምን ቢል አይገደኝም። ጭንቅላቴን ቢቆርጡኝም፡ እግዚአብሔር በአፌ ውስጥ ያስቀመጠልኝን ብቻ እናገራለሁ" አለ። እሱ ትክክል ነበር። እሱ ትክክል ነበር።

145 ዛሬም፡ ወንዶችና ሴቶች ሆይ፡ ዓለም በምታቀርብላችሁ ነገር አትወሰዱ፡ አቤት ማባበያቸው፡ የተለየ አይነት የባክቴሪ ክትባት አላቸው፡ ደግሞም እንዲህ ይላሉ፡ "ቤተክርስቲያኗን ብትቀላቀሉ፡ ሁሉም ነገር ደኅና ይሆንላችኋል።" ይህ የውሸት ክትባት ነው። ለምን? አሁንም የኃጢአት በሽታ አለባችሁ። በትክክል። ነገር ግን ወንድሜ ሆይ፡ አንድ ነገር እነግርሃለሁ፡ ይህም የኃጢአት ክትባት ይሆንሃል፡ ይኸውም፡ ወደ ክቡር የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም መጥተህ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ፡ ይህም የኃጢአት ሁሉ ክትባት ይሆንልሃል፡ ምኞቶችህም ከሰማይ ጋር የተሳሰሩ ይሆናሉ፡ ለዓለምም ነገሮች ጊዜ አይኖርህም።

እንጸልይ።

146 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ እነዚህ አባባይ መናፍስቶችን በሰዎች ላይ ስናይና፡ የእግዚአብሔርን ነገር እንደሚንቁ ስናውቅ፡ እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ እዚህ ያሉትን ወንዶችና ሴቶች ሁሉ እንድትይዛቸው፡ እጸልያለሁ። ጌታ ሆይ፡ ህይወታቸው ከቃሉ ጋር የማይስማማ መሆኑን የሚገነዘቡበት፡ ቀን ይሁን። የተሳሳተ ነገር ሲሰሙ ቆይተዋል፡ ዲያቢሎስም ባረጀ እውነተኛ ታሪክ መጽሔቶች ሲያታልላቸው፡ በማይረባ በዓለም ነገሮች፡ ባረጀ ተንቀሳቃሽ ምስል ትርዒቶች እና በርኩስ ቴሌቪዥን ሲያዝናናቸው ቆየ። አምላክ ሆይ፡ ክርስቲያን ሊያየው ያልተገባ ነገር! እግዚአብሔር ሆይ፡ ያሳምመናል። አንተም ያስታውካል፡ ልተፋህ ነው አልክ። "ውሻ ወደ ትፋቱ፡ አ—አሳማም ወደ ጭቃው ይመለሳል፡" ብለህ ተናግረሃል። ያረጀ ውሻ የሆነ ነገር ይተፋልና። በከፊል የተወለደ፡ ግብዝ ሰው፡ ወደ መሠዊያው ሲመጣ አስቡት፡ ልክ ዓለምን ሊተፋት የወደደ ይመስላል፥ በዚያውም ይቀጥላሉ፡ ዞረው ይመጡና እንደገና ይልሱታል። አምላክ ሆይ፡ ቤትህን እጽዳ፡ ጌታ ሆይ። ሃሌሉያ! የሰው የምግብ ፍላጎቱን እና ነፍሱን የሚያጸዳ መንፈስ ቅዱስ ከጥንቱ-እምነት አቋም ጋር ላክለት፡ አጽዳው የመንግሥተ-ሰማይም እሰረኛ ፍጡር አድርገው። ይሁንለት... እንደ ንስር ከፍ ከፍ ብሎ; የዚህን ዓለም ነገር እንዲያልፍ ወጣትነቱንና ቃልኪዳኑን

አድሰለት፡ ከርቀት የሚመጣውን ችግር ለማየት ወደሚችልበት ሰማይ ከፍ እንዲል አድርገው። ይሁንለት፡ ጌታ ሆይ።

147 የንሥር ዓይኖች የነበራቸው፡ ከመፈጸሙ በፊትም፡ ከፍ ወዳለው ከፍታ በርረው ነገሮችን ማየት የሚችሉ ነቢያቶችህን፡ በንሥሮች መሰልሃቸው። እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህችን ትንሽ ቤተክርስቲያን ባርካት። ወደዚህ የሚመጡትን ሰዎች ባርካቸው። ዛሬ በሮች ላይ ያሉትን እንግዶችን ባርካቸው። ይህም መልእክት ለማንም ሰው እንዳልተላለፈ እንዲያውቁ፡ ነገር ግን በተለይ፡ ጌታ ሆይ፡ በጣም ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች እንደተላለፈ ይወቁ፥ አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፍርድ ፊት አብረን መቆም እንዳለብን እናውቃለን፡ እውነትንም አውቀን ባለመናገራችን ተጠያቂ እንደምንሆን እናውቃለን። አባት ሆይ፡ በእያንዳንዱ ልብ ላይ እንዲገባ እጸልያለሁ። በኢየሱስ ስም።

148 ለእፍታ አንገቶቻችንን ዝቅ እንዳደረግን፡ እንዲህ የሚል ሰው ካለ እጠይቃለሁ፦ "ወንድም ብራንሃም፡ እነዚህ ትናንሽ ያረጁ ነገሮች ሰልችተውኛል ደክመውኛል። ለረጅም ጊዜ በእኔ ላይ የተንጠለጠሉ ትናንሽ ነገሮች አሉ። ሁሌም ሳላሰበው እ—እናገራለሁ። ማድረግ የ—የሌለብኝን ነገር አደርጋለሁ፡ ይህንንም አውቃለሁ። ይህ ለክርስቲያኖች ተገቢ አይደለም። ያንን ማድረግ አልፈልግም፥ እግዚአብሔር ያውቃል አልፈልግም። ከእንግዲኢህ ያንን ያረጀውን መንፈስ መሰማት አልፈልግም። በክርስቶስ እውነተኛ ፍቅር እና ነጻነት እንዳላገኝ፡ በሕይወቴ ሁሉ ያቆየኝ ነገር ይህ ነው። ወንድም ብራንሃም፡ እንዲትጸልይልኝ እፈልጋለሁ፡ ያ ዛ—ዛሬ ይተወኝ" የሚል ሰው ካለ። እጃችሁን ታነሣላችሁ? ሁሉም ሰው ራሱን ዝቅ ያድርግ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ኦህ፡ ማይ፡ ብዙ እጆች! ትናንሽ ያረጁ ነገሮች፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንድትጨቃጨቁ ወይም እንድትናገሩ የሚያደርጉ ትናንሽ ያረጁ ነገሮች፡ ከእንዲህ ዓይነቱ ነገሮች ጋር እንድትተባበሩ የሚያደርጓችሁ ጥቃቅን ነገሮች። ኦህ፡ ከእግዚአብሔር አይደለም። በወንድማማቾች መካከል አለመግባባት ነው። አያስፈልጋችሁም። እንዲህ አታድርጉ። ያንን እና ጥቃቅን ነገሮች ተው፡ የሚያወርዷችሁ፡ ጥቃቅን ቁጣዎችን እና ሌሎች ነገሮችን ተው።

149 እንዲህ በሉት፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ ከእንግዲህ ይህ ነገር አልፈልግም። ከእሱ የተነሳ በጣም አሞኛልና ደክሞኛል። ዛሬ ለመጣል ዝግጁ ነኝ። ጌታ ሆይ፡ ከራስ ወዳድነቴ ሁሉ መራቅ ፈልጌ፡ አሁን መጣሁ። ወንድሜ ቢበድለኛም እንኳ፡ እጸልይለታለሁ። አባቴ ቢበድለኛም እንኳ፡ እወደዋለሁ። ሚስቴ፡ ወይም ባለቤቴ ቢበድለኛም እንኳ፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ በትሕትና፡ እመላለሳለሁ። ጌታ ሆይ፡ ወደ መንግሥትህ ብቻ እመለከታለሁ። አእምሮዬ ግልጽ እንዲሆን እፈልጋለሁ። ልቤ በደስታ እንዲሞላ እፈልጋለሁ። ችግር በእውነት በዙሪያዬ ሲጮኽ፡ መሄድ እፈልጋለሁ፡ አሁንም እጆቼን ከፍ አድርጌ በንጹህ ልብ በፊትህ መቆየት እፈልጋለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ አንድ ቀን ከአንተ ጋር እንደምገናኝ፡ አውቃለሁና። እንዲህ አይነት ልምምድ እፈልጋለሁ። ጌታ ሆይ፡ ከዛሬ ቀን ጀምሮ፡ ያንን አስችለኝ" በሉት።

150 አሁን እጃችሁን ያላነሳችሁ፡ እጃችሁን ታነሳላችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። እህቴ፡ አንገታችንን ደፍተን እያለን አነስተኛ ሙዚቃ ትጫወቺልናለሽ። በእውነቱ ምን ያህል ከልባችሁ ነው? አሁን አትጫወቺ። የጨዋታ ጊዜ አይደለም። የመቀበል ጊዜ ነው። እናንተ

የምትሞሉበት ጊዜ ይህ ነው። ኑ፡ አሁኑኑ ጣሉት። ፈቃደኞች ናችሁ? ኑ፡ ያላችሁን ሁሉ ለእግዚአብሔር ስጡት። እንዲህ በሉት፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ ብዙ የለኝም። እኔ ምስኪን የቤት እመቤት ነኝ። በጣም ብዙ ማድረግ አልችልም፡ ጌታ ሆይ፡ መጽሐፍ ቅዱስህን ግን—ማንበብ እችላለሁ፡ በየቀኑ መጸለይ እችላለሁ። በአእምሮዬ ውስጥ ያለውን ቆሻሻ ሁሉ መጣል እችላለሁ። ሁሉንም ነገር ወደ ውጭ መጣል እችላለሁ። ዛሬ ጠዋት ሰባኪው በተናገራቸው በብዙ ነገሮች ጥፋተኛ ነኝ፡ ስለዚህ ዛሬ እ—እየጣልኩት ነው። አልፈልገውም። እግዚአብሔር ሆይ፡ በፍቅር ሙላኝ። መራራውን ጠላቴ እንድወድ የሚያደርገኝን ነገር ሙላኝ። በእውነት እፈልገዋለሁ፡ ጌታ ሆይ።”

151 እሷ ስትጫወት፡ አንድ አፍታ በመሠዊያው ፊት መጥታችሁ፡ ለጸሎት ቃል ከእኛ ጋር ለመሰብሰብ እዚህ ለመቆም ቅረቡ። አሁን ይህ ከልባችሁ ከሆናችሁ፡ ለመተው ዝግጁ ከሆናችሁ፡ በቅንነት ከመጣችሁ፡ ዛሬ ከዚህ መሠዊያ ያንን በልባችሁ ይዛችሁ አትመለሱም። እንዲህም በሉ፡ “እዚህ የመጣሁት ለአንድ ደቂቃ፡ ለመቆም ብቻ ነው፡ ወንድም ብራንሃም፡ አዎን፡ በግሌ፡ ከአንተ ጋር የጸሎት ቃል አደርጋለሁ።” እንድትመጡና፡ እንድትጸልዩ እ—እፈልጋለሁ። አሁን ትመጣላችሁ? እንገቶቻችሁ ዝቅ እንዳለ፡ ማነው ተነሰቶ ወደ መሰዊያው የሚመጣው፡ ማነው መጥቶ በመሰዊያው ዙርያ የሚቆመው?

አዳኝ ሆይ፡ አትለፍብኝ፡
ጸሎቴን ሰማኝ፡
ህዝብህ ጸጋህን ሲያገኝ፡
ኦህ፡ አትለፍብኝ።

አዳኝ፡ አዳኝ፡
ጸሎቴን ሰማኝ፡
ህዝብህ ጸጋህን ሲያገኝ፡
ኦህ፡ አትለፍብኝ።

152 የቱንም ያህል ክርስቲያን ብትሆኑም፡ አሁንም የሚያናግራችሁ ጥቃቅን ያረጁ መናፍስቶች አሏችሁ፡ እንድትበሳጭ ያደርጋሉ፡ ስለ ሰው እንድትናገሩ ያደርጓችኋል። አንድ ሰው መጥቶ ስለ ሌላ ሰው ማውራት ሲጀምር፡ አንተም አብረህ ትገባና፡ ኦህ፡ እንደጉድ ታወርደዋለህ። ይህ ስሕተት ነው፡ ወንድሜ። ይህን አታድርግ። በመጨረሻ ከተሰፋይቱ ምድር ውጭ ያደርግሃል። ሊኖራችሁ የማይገባ ጥቃቅን ያረጀ ነገር ካላችሁ፡ በእውነት የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችሁ ውስጥ ከሌለ፡ ሴት እና ወንድ ሆይ፡ ተነሰታችሁ መጥታችሁ፡ “እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ እዚሁ፡ ውጪ አውጥቼ እጥለዋለው። ከዚህ መሠዊያ ሌላ ሰው ሆኜ እሄዳለሁ በሉ።” እሺ ትመጣላችሁ?

153 ኢየሱስን በጭራሽ ያልተቀበለ ኃጢአተኛ አለ፡ ኃጢአተኛ እንደሆንክ የምታውቅ፡ እርሱን እንደ አዳኝህም ያልተቀበልክ ካለህ? እንዲህ በል፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አዎ፡ ብዙ ደስታ እንዳለኝ አስቤ ነበር። ወደ ጭፈራዎች እና ፓርቲዎች እና ወደ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሄጃለሁ። ትክክል ያልሆኑ ትዕይንቶችን እመለከታለሁ። የ—የተሳሳቱ ጽሑፎችንም አነባለሁ። በውስጡ ጸያፍ ታሪኮችን የያዙ የቆዩ መጽሐፍትን አነባለሁ። ሳነባቸው ያዝናኑኛል።” ወንድሜ ሆይ፡ ችግር አለብህ። ይህ የአንተ መመኘት ነው፥ እየህ፡ አንድ ሰው

ምን እንደሚያነብ፡ ምን እንደሚመለከት፡ ምን ዓይነት ሙዚቃ እንደሚሰማ እንድመለከት።

154 በቀደም፡ በመኪና እየመጣሁ፡ አንድ ሰው እጁን ዘርግቶ ሬድዮዬን አበራ፡ የሆነ የድሮ ጸያፍ ሙዚቃ ከፈተ። እኔም እንዲህ አልኩት፡ “ያንን ነገር ዝጋው። ያንን መስማት አልፈልግም።” የማይረባ ያረጀ ቡጊ-ውጊ።

“ለምን፡ መስማት እወዳለሁ፡” አለኝ።

እኔም “ተፈጥሮህ ልክ አይደለም። ተሳስተሃል፡” አልኩት።

155 ከዚያ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ እዚህ አካባቢ በነበርኩ ጊዜ፡ ተራራ ዳር ወይም ኮረብታ ላይ፡ ከሰውዬው ጋር፡ አሳ በማጥመድ ላይ ነበርኩ። ትናንሽ ወፎች እየዘመሩ። የሚያምር ድምጽ ያላቸው ወፎች ሲዘምሩ ነበር። ምስኪኑ ማርቲንጌል የሚባል ወፍ አየር ላይ ሲበር ነበር፡ ወይም ናይቲንጌል፡ ምስጋናውን እየዘመረ ይበራል። ሰውዬውን፡ ጮኬ እንዲህ አልኩት፡ “ስማ፡ ሰውዬው፡ የእኔ ዝማሬ ይህ ነው። ያንን ክፈትልኝ፡ የእኔ ሬድዮ ይህ ነው። እኔ እዚህ እያለሁ እንዲዘምሩልኝ እግዚአብሔር ይልካቸዋል። ነፍሴን ያረጋጋዋል አልኩት።”

156 ካረጁ እብድ ነገሮች ሁሉ ይሻላል፡ እነዚያ ጁክ ቦክስ ድምጾች፡ ሲለቀቁ፡ በሕዝባዊ ሰፍራዎች መመገብ እስከሚያቅታችሁ ድረስ ይጮኻሉ። ያ የዲያብሎስ አመጋገብ ነው። የዲያብሎስ ቤት ነው፡ ሁሉም በኃጢአት የተበላሸ ነው። እናንተም ወጥታችሁ በዚያ ትዝናናላችሁን? በትንሽ ሳጥኖች ውስጥ ያንን ገንዘብ ስትጥሉ፡ ያ ሁሉ የቆሻሻ ነገር ሲወጣ፡ ትደስታላችሁን? ታሳፍራላችሁ። እናንተ ባክ አድራጊዎች ናችሁ። ከአምላክ የራቃችሁ። እግዚአብሔርን አታውቁትም። እግዚአብሔርን፡ በኃጢአታችሁ ይቅርታ ብታውቁት ኖሮ፡ እንደዚህ ዓይነት የማይረባ ነገር በጭራሽ አትሰሙም ነበር። ሙት ይሆንባችኋል። ያ—ያስታውካችኋል። አትፈልጉትም። አመጋገባችሁ የተሻለ ነው። እግዚአብሔርን ትወዱታላችሁ። ዛሬ ጠዋት መጥታችሁ ከእነዚህ ከሚናዘዙት ጋር አትንበረከኩምን?

157 እዚህ ለዓመታት ክርስቲያን ሆነው የቆዩ፡ ወንዶችና ሴቶች ተንበርክከዋል። ክርስትናቸውን እያጠፋሁ አይደለም። ነገር ግን ከፍጹም ደስታ ውጪ እያደረጋቸው፡ እነሱን እያደነ ያለው፡ ዲያቢሎስ እንደሆነ ለመናገር እየሞከርኩ ነኝ። መንፈስ ቅዱስ ደስታ ነው። ወንድሜ፡ ሰክሬ እነሣለሁ፡ ሰክሬ እተኛለሁ፡ ቀኑን ሙሉ ሰክሬ እውላለው፡ ሌሊቱን ሙሉ ሰክሬ አድራለሁ። ኦህ፡ እ—እኔ ዓሣ ለ... ለማጥመድ፡ በቃ—ብቻ “አዳኝ ሆይ፡ አትለፍብኝ፡ ጸሎቴን ስማኝ።” የእግዚአብሔርን ውዳሴ እየዘመርኩ፡ አደን እሄዳለሁ። እኔ... በሄድኩበት ሁሉ፡ እሰብካለሁ። እናንተስ እንዲህ መሆን አትፈልጉምን? በመንፈስ ቅዱስ መሞላት፡ ያነቃቃል። ኦህ፡ ማይ! እነዚያን ያረጁ ቆሻሻ ዘፈኖች ሲዘፍኑ ከሰማችሁ፡ ይሄኛውን መዘመር ትችላላችሁ፥

ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ፡
ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ፥
አቤቱ ከእኔ ጋር የሚሄድ ማን ነው?
ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ።

ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ፡
ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ፥

አቤቱ ከእኔ ጋር የሚሄድ ማን ነው?
ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ።

የተባረከ ዕረፍት መቼ እወዳለሁ።
ለዘላለምስ እባረካለሁ!
የአባቴን ፊት መቼ እያለሁ፡
በእቅፋም አርፋለሁ?

ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ፡
ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ፥
አቤቱ ከእኔ ጋር የሚሄድ ማን ነው?
ወደ ተስፋይቱ ምድር ጉዞ ላይ ነኝ።

158 መጥታችሁ፡ አብራችሁ አትሄዱም? አምስት መቶ ገደማ የምንሆን ሰዎች ቆመን አንድ መቶ ሀያ ሰዎችን እያጠመቅኩ ሳለ፡ በዚህኛው የዓመቱ ወቅት፡ እዚህ ወንዙ ዳርቻ ላይ ሳጠምቅ፡ ታላቁ የንጋት ኮከብ በወንዙ ላይ ሲበራ አስታውሳለሁ። ሃሌሉያ! “አንድ ቀን ወንጌልን በመላው ዓለም ማሰራጨት ትጀምራለህ፡” የሚል፡ ድምፅ ተሰማ። አንድ ምስኪን፡ ድሃ፡ ምንም የማያውቅ ገበሬ ልጅ እንዴት እንዲህ ሊያደርግ ቻለ? የእግዚአብሔር ጸጋ! አሜን።

159 አቤቱ፡ ማን መጥቶ ይሄዳል? አሁን ሸክማችሁን ሁሉ፡ አስወግዱ፡ አጥፉ። አባባይ መናፍስትን አትስሙ። የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ሲባል፡ ኑ፡ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ! “ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፡ ይጠግባሉና።”

160 በመሠዊያው ላይ ከእነዚህ ጋር እየጸለይን ሳለ ራሳችንን ዝቅ እናድርግ።

ውድ ልጆቼ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ሸክማችሁን ለማስወገድ፡ ወደዚያ እንደመጣችሁ አስታውሱ። እያንዳንዱን ሸክም ወደ ጎን በመተው ቶሎ የሚከበውን ሃጥያት ለማስወገድ መጥታችኋል። ጳውሎስ፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 12፡ ተናግሯል።

... እነዚህን የሚያህሉ **ምስክሮች** እንደ **ደመና በዙሪያችን... ካሉልን፡ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ፡ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት**... **አስወግደን**፥...

**እንግዲህ ምን እላለሁ?** ስለ... **ጌዴዎንና ስለ፡...** ባርቅ **ስለ... ሶምሶንም፡... ስለ ዮፍታሔም፡ ስለ፡... ዳዊት፥ ስለ ሳሙኤልም**... **ስለ ነቢያትም፡ እንዳልተርክ ጊዜ ያጥርብኛልና፥**

**እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፡ ጽድቅን አደረጉ፡ የተሰጠውን** የተስፋ ቃል **አገኙ፡** የአንበሶችን አፍ **ዘጉ፡**

**የእሳትን ኃይል አጠፉ፡ ከሰይፍ ስለት አመለጡ፡ ከድካማቸው** በረቱ **በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፡** ጠላትን በሰልፍ... **የባዕድ**... **ጭፍሮችን** አባረሩ...

ሴቶች **ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ...**

**ሌሎችም** ተሰቃዩ፡ **መዘበቻ ሆኑ** ተገረፉ፡... **እንዲሁም፡** ከዚህም በላይ፡ **ወኅኒ እና እሰራት፥**

**ሌሎች——ም** መዘበቻ **በመሆንና** በመገረፍ... ከዚህም በላይ... ተፈተኑ...

… እነዚህም ሁሉ **በእምነታቸው ተመሰክሮላቸው፡…**

እነዚህም **ሁሉ፡ በእምነታቸው ተመሰክሮላቸው ሳሉ፡ የተሰጠውን የተሰፋ ቃል አላገኙም፥**

ያለ እኛ ፍጹማን እንዳይሆኑ፡ **እግዚአብሔር ስለ እኛ አንዳች የሚበልጥ ነገርን አስቀድሞ አይቶ ነበርና።**

**እንግዲህ** እነዚህን የሚያህሉ **ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን እንዳሉ… ተገንዝበን፡ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ፡ ቶሎም የሚከበንን ኃጢአት… አስወግደን፥** የእምነታችንንም **ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፡**

**በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ፥ እርሱ ነውርን** ንቆ፡ **በፊቱም ስላለው ደስታ በመስቀል ታግሦ፡ በ… እግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።**

161 ኢየሱስ፡ ሲጸልይ፡ "አባት ሆይ፡ ራሴን እቀድሳለሁ፡" አለ። ኢየሱስ ለቤተክርስቲያን፡ የተቀደሰ ሆነ። ማግባት ይችል ነበር፡ ግን አላደረገውም። የተቀደሰ ሆነ። "ቃልህ እውነት ነው። አባት ሆይ፡ በእውነት፡ ቀድሳቸው፡" ብሏል።

162 አሁን ሸክምን ሁሉ እናስወግድ። ቁጣ አለባችሁን? መናገር በማይገባህ ጊዜ እንድታወራ የሚያደርግ፡ የሆነ ነገር አለብህን? አምላክ ሆይ! አሁን ጣሉት። ጣሉት፡ የመሠዊያው እሳት ሲወርድ እና ሲወስደው ተመልከቱ። የእግዚአብሔር ፍቅር ሲልሰው ታያላችሁ። ያረጀ ራስ ወዳድነት ሁሉ፡ ከሚስትህ ጋር ስታወራ፡ ከባልሽ ጋር የምታወሪበትን መንገድ ተመልከቺ፡ ከጎረቤት ጋር የምትናገሩበት መንገድ፡ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሰዎች ጋር የምትናገሩበት መንገድ፡ ዛሬ ጠዋት በመሠዊያው ላይ ጣሉት፡ የእግዚአብሔርም እሳት ወርዳ ትወስዳለች፡ መለኮታዊም ፍቅርም ባለበት ያነደዋል።

163 በሽታ አለባችሁ? በመሠዊያው ላይ አኑሩት፡ እንዲህ በሉ፡ "ጌታ ሆይ፡ እነሆ። ንፁህ መንፈስ ፍጠርልኝ። የፈውስ ኃይልን ፍጠርልኝ።" እግዚአብሔር የሚያደርገውን ጠብቁ። እግዚአብሔር ዛሬ ጠዋት ያደርገዋል።

164 በሰማይ የምትኖር አባታችን ሆይ፡ በመሠዊያው አጠገብ ያሉትን በመወከል፡ በፊትህ እነሰግዳለን። አባት ሆይ፡ ጸጋህ በእያንዳንዳቸው ላይ ይረፍ። አሁን… ጌታ ሆይ፡ ስለ እነርሱ እኔ መጣል አልችልም። ራሳቸው መጣል አለባቸው። ማንም ሰው ሊጥልላቸው አይችልም። ብቻቸውን መጣል አለባቸው። ነፍሶቻቸው በውስጣቸው እንዲህ ትበል፡ "እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህ ቁጣ፡ ጌታ ሆይ፡ እዚህ እጥለዋለሁ። መልሼ መቼም አላነሳውም። ማንም ይምጣ ወይም ይሂድ፡ ከአሁን በኋላ፡ እጥለዋለሁ። ከብዙ ሔሜት ጋር ለመወገን ቀላል የነበረው ይህ አንደበቴ፡ እዚሁ እጥላለዋለሁ፡ ጌታ ሆይ። ዳግመኛ አላነሳውም። ጌታ ሆይ፡ አንደበቴን ቀድሰ። ኢሳያስ 'ከንፈሮቼ የረከሱብኝ ሰው ነኝ። ወዮልኝ!'" ባለ ጊዜ፡ መላእክቱ እንዳለፉ እንዲሁ ይሰማኝ፡ መልአኩም መጥቶ፡ የእሳት ጉጢት ወስደና፡ ወደ መሠዊያውም ሄዶ የእሳት ፍም ያዞ፡ ከንፈሮቹም ዳሰሰና ቀደሰው። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት፡ ስህተት የሚናገር፡ እና ጠብን የሚዘራውን ተናጋሪ ሁሉ ቀድሰው። ይሁንለት፡ ጌታ ሆይ።

165 በዚህ ሕንፃ ውስጥ የተንበረከኩ በሽተኞች ሁሉ፡ የታመሙ ሰዎች ሁሉ፡ በሽታም፡ አጋንንት መሆኑን እውቀውታል። እግዚአብሔር ሆይ፡ እንደ አገልጋይህ፡ በኢየሱስ ስም፡ እገሥጻቸዋለሁ። ከታመመ ሰው ሁሉ ይውጡ። እንዲሁም ርኩስ የሆነ፡ ሰው ሁሉ፡ ርኩስ የሆነ ሃሳብ ያለው፡ ተራ የሆነ፡ ምኞት ያለው፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች፡ እግዚአብሔር፡ ከውስጣቸው ያውጣ። እነዚህ ሁሉ እዚህ ሲጋራዎችና፡ ትንሽ ማህበራዊ መጠጦችን፡ ትንሽም ፓርቲዎችን፡ ራስ ወዳድ ነገሮችን ለማስወገድ እየሞከሩ ነው፥ እግዚአብሔር ሆይ፡ እነዚያ ነገሮች ከአሁን በኋላ ምንም ፍላጎት እንዳይኖራቸው ልባቸውን በመንፈስ ቅዱስ አንቃቃው። ያን ጊዜ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ሙላት የተነሣ፡ ክፍት ቦታ አይገኝባችሁም።

166 እግዚአብሔር ሆይ፡ ይህችን ትንሽ ቤተክርስቲያን የሚቃጠል ቁጥቋጦ አድርጋት። መንፈስ ቅዱስ የሚኖርባት እንድትሆን አድርጋት፡ ዓለም የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት የሚዞርባት፡ የምትነድ እሳት አድርጋት። እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት እዚህ ካሉት ሁለት መቶ የሚጠጉ፡ በጥቂት ሰዎች ጀምር። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ።

167 ሁሉንም ልብ፡ እያንዳንዱን ሜቶዲስት፡ እያንዳንዱ ባፕቲስት፡ እያንዳንዱን ካቶሊክ፡ እያንዳንዱን ፕሪስባይቴሪያን፡ እያንዳንዱን ጴንጤ ቆስጤን አጽዳ። ጌታ ሆይ፡ ከልባቸው አውጣው፡ ዛሬም ወደ አንተ ይምጡ። ይሁንልን፡ አባት ሆይ። ለአንተ አቀርባቸዋለሁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ነፍሳቸውን ለማንጻት፡ እና ለሥጋቸው ፈውስ አደራ እሰጣቸዋለሁ። አሜን።

168 በመሠዊያው ላይ፡ ሸክማችሁን አስቀምጣችሁ እንደሆነ እጠይቃለው? እዚያ እንደተቀመጠ ይሰማችኋል? እዚያ እንደተቀመጠ ከተሰማችሁ፡ እናንተ ራሳችሁ ፍረዱ። የምትጸልዩት እናንተ ናችሁ። ስብከቱን ጨርሻለሁ። ጸሎቱን እናንተ አድርጉት። ወንድም፡ እህት ሆይ፡ የቀረ ሸክም አለባችሁ? በእውነቱ እዚያ መጣል ትችላላችሁን? ከቻላችሁ እጃችሁን አውጡና፡ እንዲህ በሉ፡ “አዎን፡ አምላኬ ሆይ፡ እዚሁ ጥያለሁ። መጥፎ ነገሬ ሁሉ፡ በመሠዊያው ላይ እጥላለሁ።” እዚህ በመሠዊያው፡ መጨረሻ ላይ፡ በቀኙ፡ እመቤቴ? እዚያ መጣል ትችያለሽን? ያንን ያረጀ ሸክም መጣል ትችያለሽን? እንዲህ በይ፡ “አዎን፡ አንተ የቀራንዮ በግ ሆይ፡ እምነቴ ወደ አንተ ይመለከታል።” ሁላችንም አንድ ላይ እንዘምር።

እምነቴ አንተኑን ያያል፡
አንተኑን የቀራንዮውን በግ፡
ሰማያዊ አዳኝ ሆይ፡
ጸሎቴን አሁን ሰማኝ፡
ኩነኔ አሁን አንሳልኝ፡
አቤቱ ዛሬ ፍቀድልኝ
የአንተው ሰው አርገኝ!

169 በእግራችን እንቁም፡ እውነተኛ ትህትና፡ ሁሉም ሰው ይቁም። አሁን ሁላችሁም፡ በጥሞና አዳምጡ። ማንም ሰው እንዳይሄድ። ልክ… አገልግሎቱ አልተጠናቀቀም። ይህ ቅድስና፡ እና አክብሮት እንዲኖራችሁ እፈልጋለሁ።

በህይወት ድንግዝግዝ ስጓዝ፡

ሀዘን በዙርያዬ ሲዘረጋ፡
አንተኑ መሪ ሁነኝ፡
ጨለማን ገፈህ ብርሃን አርግልኝ፡
የሀዘንን እንባ አብስ፡
ዛሬ ፍቀድልኝ
የአንተው ሰው አርገኝ!

አሁን ለጎረቤታችሁ አትዘምሩ። ዓይኖቻችሁን ጨፍኑ፡ እና እጆቻችንን ወደ እግዚአብሔር አንስተን፡ ቀስ ብለን እንዘምር።

በህይወት ድንግዝግዝ ሰዓዝ፡
ሀዘን በዙርያዬ ሲዘረጋ፡
አንተኑ መሪ ሁነኝ፡
ጨለማን ገፈህ ብርሃን አርግልኝ፡
የሀዘንን እንባ አብስ፡
እንድሰት አትፍቀድ
ከጎንህ አልራቅ።

አባት አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
አባት አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
አባት አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
ከአድማስ ተሻግር።

ኦህ፡ አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
ከአድማስ ተሻግር።

ኦህ፡ አንዷ ቀን ነገ ትሁንልኝ፡
አንዷ ቀን ነገ ትሁንልኝ፡
አንዷ ቀን ነገ ትሁንልኝ፡
ከአድማስ ተሻግር።

170 በሌላኛው ምድር አባት ያላቸው፡ ስንት ናቸው ብዬ አሰባለሁ? እስቲ እጃችሁን ልመልከት። በሌላኛው ምድር እናት ያላችሁ ስንት ናችሁ? እስቲ እጃችሁን ልመልከት። በሌላ ምድር አዳኝ ያላችሁ ስንት ናችሁ? እስቲ እጃችሁን ልመልከት።

እንዴት ያለ አስደሳች ስብሰባ ይሆናል!
እንዴት ያለ አስደሳች ስብሰባ ይሆናል!
እንዴት ያለ አስደሳች ስብሰባ ይሆናል!
በሌላኛው...

171 አንድ ነገር እንድታደርጉ እፈልጋለሁ። አሁን ያንን እንደገና ስንዘምር፡ ከጎናችሁ ከሚቆመው ሰው ጋር እጅ በመጨባበጥ፡ “ወንድም፡ እኅት፡ ስለ እኔ ጸልይ፡ በሌላ ምድር እንደንገናኝ፡” እንድትሉ እፈልጋለሁ። ከልባችሁ ካልሆነ አታድርጉ። ስንቶች መገናኘት ትፈልጋላችሁ? በዚያ ማዶ፡ መገናኘት የምትፈልጉ ስንቶች አላችሁ? አዎን፡ ሁላችንም እንፈልጋለን። አሁን እርስ በርሳችን እንጨባበጥና፡ እንዲህ እንበል፡ “ወንድሜ፡ ላገኝህ እፈልጋለሁ።

ከአድማስ ባሻገር ላገኝህ እፈልጋለሁ።" አሁን ይህን ስንዘምር፡ "አንድ አዳኝ አለኝ።" መልካም።

አዳኝ አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
አዳኝ አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
አዳኝ አለኝ ከአድማስ ማዶ፡
ከአድማስ ተሻግሮ።

ኦህ፡ አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
አንድ ቀን እሱን ለማየት እሄዳለሁ፡
ከአድማስ ተሻግሮ።

172 ጥሩ እና መልካም ስሜት እንዲሰማችሁ አያደርግም? (**ኢየሱስ ሆይ፡ ከመስቀሉ አጠገብ ጠብቀኝ**።)

ኢየሱስ ሆይ፡ ጠብቀኝ...
ውድ ምንጭ ባለበት፡
የፈውስ ምንጭ፡ ለሁሉ ነጻ፡
ከቀራንዮ ምንጭ ይፈሳል።

ሁላችሁም እጃችሁን አንሱ።

መስቀል ስር፡ መስቀል ስር፡
ክብሬ ሁን ለዘላለም፡
ነፍሴን በንጥቀት ቀን
ከወንዙ ማዶ እስክታርፍ ድረስ።

መስቀል ስር፡ መስቀል ስር፡
ክብሬ ሁን ለዘላለም፡
ነፍሴ በንጥቀት ቀን
ከወንዙ ማዶ እስክታርፍ ድረስ።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ስለገዛ
በቀራንዮ ላይ።

እግዚአብሔር ይመስገን!

173 አሁን ዝም ብለን አንገታችንን እናጎንብስ። በተመቸን መንገድ፡ እጃችንን ወደ ላይ ከፍ አድርገን እናመስግነው፡ እንደዚህ እያልን፡ "ነፍሴን ስላዳንካት፡ አመሰግንሃለሁ፡ ጌታ ሆይ። ሙሉ ስላደረከኝ፡ አመሰግንሃለሁ፡ ጌታ ሆይ። ስላደረግኸው ሁሉ፡ ስለ መልካሙ እርነት፡ ስላመጣኸው መዳን፡ ጌታ ሆይ፡ አመሰግናለው። አመሰግንሃለሁ፡ ጌታ ሆይ።"

ይህን የምስጋና-መስዋዕት እንሰጥሃለን። ፍቅር ስለሆንክ እናመሰግንሃለን። የቆላ አበባ ነህ፡ የንጋት ኮከብ፡ የሳሮን ጽግረዳ፡ ሁሉም-በ-ሁሉም የሆንክ ነህ። አንተ አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ ነህ፡ የነበረውና፡ ያለው፡ የሚመጣውም፣ ታላቁ አልፋ፡ ኦሜጋ አንተ ነህ። አንተ ድንቅ ነህ፡ የሰላም አለቃ፡ የዳዊት ሥር እና ዘር ነህ። አንተ ሁሉንም ነህ! ጌታ ሆይ፡ ስላደረግኸው ሁሉ፡

እናመሰግንሃለን። ለመንገዳችን ብርሃን ነውና፡ ስለ ቃልህ እናመሰግናለን። ኦህ፡ ጌታ ሆይ፡ በብርሃን እንድንሄድ እንድትፈቅድልን፡ እንጸልያለን። ይሁንልን፡ አባት ሆይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

መልካም። አንድ ደቂቃ ተቀምጠን ሳለ። (**በብርሃን ውስጥ እንሄዳለን**።)

በብርሃን ውስጥ እንሄዳለን፡ በሚያምር ብርሃን፡
የርኅራኄ ጠብታዎች ብሩህ ወደሆኑበት ኑ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን...

174 ኑ፡ ቅዱሳን፡ አብረን እንዘምር!

በብርሃን ውስጥ እንሄዳለን (ንጽህና፡ ቅድስና)፡ በሚያምር ብርሃን፡
የርኅራኄ ጠብታዎች ብሩህ ወደሆኑበት ኑ፥
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

ና፡ ንጉሥህ እንደሆነ እምነህ ተቀበለው፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን፥
ያኔ የሰማይ ደወሎች ይደውላሉ፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

ሁሉም ሰው!

በብርሃን ውስጥ እንሄዳለን (ለመንገዴ ብርሃን)፡ በሚያምር ብርሃን፡
የርኅራኄ ጠብታዎች ብሩህ ወደሆኑበት ኑ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

175 ጥሩ ስሜት እንዲሰማችሁ አያደርግም? ሰንቶቹ ጥሩ ስሜት ይሰማቸዋል? አሁን እጅ ብቻ አንሱ፡ እንዲህ በሉ፡ "ጥሩ ስሜት ይሰማኛል።" መንፈስ ቅዱስ ሁላችሁም ጠራርጎ አውጥቶአችኋል። ከዚያም (ምን? ) በብርሃን ውስጥ እንጓዛለን። ማንንም አትሰሙ... ብርሃኑ ምንድን ነው? "ቃልህ መብራት ነው።" ከዚያስ፡

በብርሃን ውስጥ እንሄዳለን፡ በሚያምር ብርሃን፡
የርኅራኄ ጠብታዎች ብሩህ ወደሆኑበት ና፣
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የ...

176 አሁን፡ አይደንቅም ወይ? ዝም ብለን መዝጋት የምንችል አይመስልም። መንፈስ ቅዱስ ይዞናል! እንዲሁ አይሰማቹም? ልክ... ? ... ልክ እየወጣ ያለ ይመስላል።

... ወንጌል በደም የተሞላ ነው፡
ለእውነት ሲሉ የሞቱ ደቀ መዛሙርት ደም፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል በደም የተሞላ ነው።

ለዚህ መንፈስ ቅዱስ እቅድ ለመሞት የመጀመሪያው ሰው፡
መጥምቁ ዮሐንስ ነበር፡ ነገር ግን እንደ ሰው ሞተ፥
ከዚያም ጌታ ኢየሱስ መጣ፡ ሰቀሉት፡
መንፈስ ሰዎችን ከኃጢአት እንደሚያድናቸው ሰበከ።

ጴጥሮስና ጳውሎስ፡ እና ዮሐንስ፡
ይህ ወንጌል እንዲያበራ ሕይወታቸውን ሰጡ፥
እንደ ቀደሙት ነቢያትም፡ ደማቸውን አፈሰሱ፡
የእግዚአብሔር ቃል በእውነት እንዲነገር ደማቸውን ቀላቀሉ።

እስጢፋኖስን ወገሩት፡ ኃጢአትን በመቃወም የሰበከ፡
ራሱን በድንጋይ ሰበሩት፡ ቁጣቸው ስለነደደ፥
ነገር ግን በመንፈስ ሞተ፡ መንፈሱንም ተወ፡
ህይወት-ሰጪ ወደ ሆነው ሄደ፡ ከሌሎቹ ጋር ለመሆን።

በደም መሞላቱን ይቀጥላል፡ አዎን፡ በደም መሞላቱን ይቀጥላል፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል በደም የተሞላ ነው፡
ለእውነት ሲሉ የሞቱ ደቀ መዛሙርት ደም፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል በደም የተሞላ ነው።

አዳምጡ!

ከመሠዊያው በታች ነፍሳት አሉ፡ "ምን ያህል ጊዜ፡" ይጮኻሉ?
ጌታ በደል የሠሩትን እንዲቀጣ፥
ነገር ግን የሕይወታቸውን ደም የሚሰጡ ብዙ ይሆናሉ
ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ከቀይ ጎርፍ ጋር።

በደም መሞላቱን ይቀጥላል፡ (ሃሌሉያ!) በደም መሞላቱን ይቀጥላል፡

ከነሱ አንዱ መሆን እፈልጋለሁ።

... የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል፡ በደም የተሞላ ነው፡
ለእውነት ሲሉ የሞቱ ደቀ መዛሙርት ደም፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል በደም የተሞላ ነው።

177 በቀጥታ ከመድረክ ላይ መሄድ እፈልጋለሁ። አሜን። ኦህ፡ እንዴት ድንቅ ነው! ወንድሞቹ የሕይወታቸውን ደም ሰጡ። የበለጠ ተመሳሳይ ነገር ይደረጋል። አታስቡ። በቅርቡ ወደ ትርኢት እየመጣ ነው። ወይ ትገባላችሁ ወይም ትወጣላችሁ። አሁን ሁሉም በአብያተ ክርስቲያናት ካውንስል ውስጥ፡ ተቀላቅለዋል ሁሉም ወደ ውስጥ እየገባ ነው። ሁሉም በአንድ ላይ እየተሰባሰቡ ነው።

ነገር ግን የሕይወታቸውን ደም የሚሰጡ ብዙ ይሆናሉ፡
ለዚህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ከቀይ ጎርፍ ጋር።

በደም የተሞላ ነው፡ አዎን፡ በደም የተሞላ ነው… (ኦህ፡
  ሃሌሉያ!)
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል በደም የተሞላ ነው፡
ለእውነት ሲሉ የሞቱ ደቀ መዛሙርት ደም፡
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል በደም የተሞላ ነው፡

178 ማይ! መነጠቅ ከቤተክርስቲያኑ በላይ እንደሆነ ይሰማኛል። ኦህ፡ በጣም ደስ ደስ ይለኛል! ኃጢአቶች ሁሉ ከደሙ በታች ናቸው። አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ይወዳል። የመንፈስ ቅዱስ ምግብ ቃል ነው፡ አያችሁ። ኦህ፡ ማይ! ይወርዳል እና በሰዎች መካከል ይደርሳል፡ ኃጢአታቸውን ያጸዳል፡ ሕመማቸውን ያሰወግዳል፡ ድብርታቸውን ያሰወግዳል። አሁን ሰክሬአለሁ፡ ከአቅም በላይ ሰክሬአለሁ፡ በመንፈስ ሰክሬአለሁ፡ ልቤን ማቅረብ እወዳለሁ። ማንም ሰው ምንም ቢበድል፡ ይቅርታ ተደርጎለታል። በጣም መራራ ጠላትህ፡ ሁሉም ነገር አልቋል። ማንም ተናግሮ ወይም ምንም ብሎ ቢሆን፡ እ… ደህና፡ ሁ… ሁሉ ጠፍቷል፡ ሁሉም አሁን ጸድቷል።

እና በደም ይንጠባጠባል፡ አዎ፡ በደም ይንጠባጠባል፡
የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል ደም ያንጠባጥባል።
ስለ እውነት የሞቱ ደቀ መዛሙርት ደም፣
ይህ የመንፈስ ቅዱስ ወንጌል…

ኦህ፡ ማይ! እንዴት ድንቅ ነው!

እንዴት አስደናቂ ጊዜ ነው ለእናንተ፡
እንዴት አስደናቂ ጊዜ ነው ለእኔ፥
ሁላችንም ንጉሣችንን ኢየሱስን ለመገናኘት ከተዘጋጀን፡
እንዴት ያለ አስደሳች ጊዜ ይሆናል።

አስደናቂ ጊዜ ለእናንተ፡
አስደናቂ ጊዜ ለእኔ፥
ሁላችንም ንጉሣችንን ኢየሱስን ለመገናኘት ከተዘጋጀን፡
እንዴት ያለ አስደናቂ ጊዜ ይሆናል።

ወደዳችሁት? እስኪ፡ አንድ ላይ!

ኦህ፡ አስደናቂ ጊዜ ለእናንተ፡
አስደናቂ ጊዜ ለእኔ፥
ሁላችንም ንጉሣችንን ኢየሱስን ለመገናኘት ከተዘጋጀን፡
እንዴት ያለ አስደናቂ ጊዜ ይሆናል።

179 ልክ እንደ ጥንቱ-ሪቫይቫል ዓይነት ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳለ ይሰማኛል። አይደል? ልክ እንደ ጥንቱ ማጽዳት፡ በደንብ የሚያጥብ፡ ጥሩ፡ የጥንቱ አስደናቂ ጊዜ። ጥሩ ስሜት አይሰማችሁም? ኦህ!

አመሰግነዋለሁ፡ አመሰግነዋለሁ፡
ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመሰግኑት፥

አሁን ሁላችሁም እንዘምር። ታውቁታላችሁ? እኔ አውቀዋለሁ። ና ወደዚህ፡ እንድመራው እርዳኝ፡ ወንድም ኔቪል። እና ሁላችሁም፡ አንድ ላይ አሁን፡ ከቻላችሁ እጃችንን እንስተን፡ አሁን፡ አሁን፡ ከቻላችሁ፡ ዘምሩ።

ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑ፡
ሰዎች ሆይ፡ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

180 አሁን፡ እሰቲ፡ ሁላችሁም!

አመስግነዋለሁ፡ አመስግነዋለሁ፡
ስለ ኃጢአተኞች የታረደውን በግ አመስግኑት፡
ሰዎች ሆይ ሁላችሁ ክብር ስጡት፡
ደሙ ዝገትን ሁሉ አስወግዷልና።

ኣሜን። አይደንቅም ወይ?

... በዕንቁ ነጯ ከተማ፡
ቤት፡ መሰንቆና፡ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥
አሁን ነቅቼ እየጸለይኩ፡ እጠብቃለሁ፡
ዮሐንስ ስትወርድ ያያት ነጯ ከተማ።

181 አሜን። ድንቅ ነው! ኦህ! አሁን ሁላችሁም፡ በእግራችን እንቁም። ጥሩ ስሜት እንደሚሰማችሁ ተሰፋ አደርጋለሁ። ዛሬ ማታ አገልግሎቶቹን አስታውሱ። አሁን የጥንቱ ቆንጆ የሰንብት ዝማሬ እንዘምራለን።

ለኢየሱስ ስም ሰገዱ፡
በእግሩ ስር ውደቁ፡
የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ያጠልቃል፡
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

በጣም ጥሩ። ሁሉም አሁን፡ አንድ ላይ። በጣም ጥሩ።

ለኢየሱስ ስም ሰገዱ፡
በእግሩ ስር ውደቁ፡
የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ያጠልቃል፡
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

ድንቅ ስም (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ነው! (ኦህ ውብ ነው!)
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደስታ፡
ድንቅ ስም (ድንቅ ስም!) ኦህ ውብ ነው! (ኦህ ውብ ነው!)
የምድር ተሰፋ የሰማይ ደስታ።

182 ማለዳው እንዴት ድንቅ ነው! እንዴት ያለ አስደናቂ ጊዜ ነው! አሁን ለአፍታ ብቻ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። አሁን ሁላችሁም፡ ወደ ክርስቶስ ወደ አዳኛችሁ ተመልከቱ። በዝምታ፡ ምስጋና እና ውዳሴ እንድትሰጡት እፈልጋለሁ። እንዲህ በሉት፡ "ጌታ ሆይ፡ ነፍሴን ስለቀደስከኝ አመሰግንሃለሁ። ስላደረግክልኝ ነገር ሁሉ አመሰግንሃለሁ። ጌታ ሆይ፡ መንፈስህ ቀን በቀን በእኔ ላይ ይሁን። ምራኝ። መንገድ አሳየኝ። ባርከኝ" እግዚአብሔር ያን በረከት እንዲሰጣችሁ፡ ጸሎቴ ነው።

አሁን አንገታችንን ዝቅ አድርገን፡ ወንድም ኔቪል፡ በጸሎት ቃል ይዘጋልናል።

55-0724 አባባይ መናፍስቶች
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org